# ሐመር


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣
ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት
ጠብቆ የሚወጣ

ነሐሴ/ ፳፻፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመትና
ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ዋና ክፍል
በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ
ትምህርታዊ መጽሔት




## ማውጫ


የማኅበሩ መልእክት
ችግሮች የሚወገዱበት አውጥተን ስንነጋገርባቸው እንጂ
፪

ዐውደ ስብከት
ሶ-ባኤ
፬

ትምህርተ ሃይማኖት
፰

ዐቢይ ጉዳይ
ክብረ ክህነት
፲፫

እናስተዋውቃችሁ
ቶማስ ዘመርዓስ
፲፱

የጥያቄዎቻችሁ መልስ
፳፯

ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት
"ደካሞችን አጠቃም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁላቸው"
፳፬

ኪነ ጥበብ
ነፍሴን የት ልውሰዳት!
፴

ከዓለም ማዕዘናት
የቱርክ መንግሥት የሀግያ ሶፊያን ቤተ መቅደስ
፵፫

አቦጊዳ የግእዝ ትምህርት
ቅጽል
፵፭


"ማኅበረ ቅዱሳን" እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይኽን ስያሜ አግኝቷል።


## የዝግጅት ክፍሉ

ስልክ ፲፩-፰-፩፪-፪፰-፬፱
ፖ.ሣ.ቁ ፰፲፲፯፰
ኢ-ሜይል magazine@eotcmk.org
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት ስልክ
፲፩-፩-፭፭-፫፪-፫፱
የልማት ተቋም የስርጭት ክፍል ስልክ
፲፩-፩-፪፫፬፭-፪፱
የማስታወቂያ ዝግጅት ክፍል ስልክ
፲፱፬፪-፫፰-፩፯-፱፩

**ም/ዋና አዘጋጆች**

ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ
አድራሻ፡- ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ
ወረዳ ፲፭ የቤት ቁ. ፯፪፲

**ከፍተኛ ሪፖርተር**

ዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን

**ሌይ አውት ዲዛይነር**

ግደይ ገብሬ

**ጸሓፊ**

ገነት ታደሰ

# ችግሮች የሚወገዱት፣ አውጥተን ስንነጋገርባቸው እንጂ፣ ስንሸፋፍናቸው አይደለም!

## የማህበሩ መልእክት

በመንፈሳዊ ሕይወታችንም ሆነ በማኅበራዊ ኑሮአችን እያደግንና እየጠነከርን መሄድ የምንችለው፦ በየጊዜው የሚያጋጥሙንን ጥፋቶችና የወደቅንባቸውን ችግሮች በትክክለኛው መንገድ በመለየት ተጸጽተን ለዘለዓለማዊ ሕይወታችን ንስሓ ስንገባ፣ ለማኅበራዊ ችግሮቻችንም ተጠብበንና ተጨንቀን መፍትሔ የምንፈልግ ስንሆን ነው።

ማኅበረሰባዊ ለሆኑ ችግሮች መፍትሔ በምንሻበት ጊዜም በተቻለን መንገድ የምንመርጣቸው ስልቶችና መንገዶች፣ ሁል ጊዜም መልካምና ለችግሩ አግባብነት ያላቸው እንዲሆኑ የሚጠበቁ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ፣ እንደየግል ግንዛቤአችን የምንሄድ ከሆነ ወደምንፈልገው ግብ የማያደርሱን ወይም በተቃራኒው ችግሩን የሚያባብሱ ወይም ችግሩን ለጊዜው የጠፋ በሚመስል መንገድ በማዳፈን፣ በኋላ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ይዘው ሊመጡ ይችላሉ። ይህም ጊዜያዊ የሆነ ፋታን በመፈለግ መሠረታዊ የሆነውን ችግር ከነምክንያቱ ለመስማት፣ ለማወቅና ለመናገር፣ ብሎም ለመፍትሔው አቅማችን በፈቀደ መጠን ኃላፊና ባለድርሻ የመሆን ግዴታ ያለብን መሆኑን ከፍ ያለ ዋጋ ካለመስጠት ሊመጣ የሚችል ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘም በአሁኑ ዘመን በሀገራችን ውስጥ ሕገ ወጥና ኢ-ሰብአዊ በሆኑ ድርጊቶች ምክንያት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ላይ በተለየ ሁኔታ እየደረሰ ያለውን ግድያ፣ ሰቆቃና በእምልኮ ነፃነት ላይ የሚደረግ ክልከላ፣ የንብረት ውድመትና ቃጠሎን አላየንም፤ አልሰማንም፤ በድንገት የተፈጠረ ነው፤ ወይም ጉዳቱና ጥፋቱ የተለየና ምንም አይደለም! ብለን ማለፍ የማንችለው ነው። ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ በኦርቶዶክስ ምእመናን ላይ ታቅደው እየተፈጸሙ ያሉ ድርጊቶችን ስንመለከታቸው፦ ሰበባቸው ምንም፣ ይሁን ምን፣ ለጥቃቶቹ ዒላማ የሚደረጉት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ምእመናኗ መሆናቸውን ለማስረዳት በተደጋጋሚ ሲፈጸሙ የቆዩ ሕገ ወጥ ድርጊቶችን በአስረጂነት በማቅረብ ማረጋገጥ ይቻላል።

ለምሳሌም በቅርቡ፦ ሰኔ ፳፪ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመን የሆነው አርቲስት ኃጫሉ ሁንዴሳ፣ የፖለቲካ ተልእኮ ባላቸው ሰዎች ከተገደለ ከሰዓታት በኋላ፣ ለብዙ ወራት ዝግጅት የተደረገበት በሚመስል ሁኔታ፦ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የተለያዩ ቦታዎች በሚኖሩ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ላይ የተፈጸመው ግድያ፣ የአካል ጉዳት፣ ማሳደድና ሰቆቃ እንዲሁም የንብረት ውድመትና ቃጠሎ፣ ከዓይነ ኅሊናችን ያልጠፋ፣ ግዙፍነት ያለው ማሳያ ነው።

እነዚህን የሰቆቃ ሥራዎች በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ላይ የፈጸሙት ቡድኖችና ግለሰቦች ከተጐጂ ወገኖቻችን ጋር በአንድ አካባቢ የተወለዱ፣ያደጉና የሚኖሩ፣ በአንድ መንግሥት የሚተዳደሩ፣ እናትና አባት፣ የሃይማኖት መሪም ያላቸው፣ ኢትዮጵያውያን እንጂ፤ ሃይማኖትና የሃይማኖት መሪ፣ ባህልና ትውፊት የሌላቸውና ከውጭ የመጡ የሌላ ሀገር ሰዎች አልነበሩም። በእውነት እንነጋገር ከተባለ፦ የሀገራችን ሕዝብ በሃይማኖት፣ በመፈቃቀርና በመከባበር የሚኖር፣ የወላጆችና የልጆች ግንኙነት እንደ ምዕራባውያን ያልሆነ፣ ማኅበራዊ መተሳሰብን የሚያጠናክሩ ባህላዊ ሁኔታዎች ባልጠፉበትና ሕግን ለማስከበር በየደረጃው የተዋቀሩ የመንግሥት አካላት ባሏት ሀገር ውስጥ፣ ሃይማኖትን ምክንያት በማድረግ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ላይ ለተፈጸሙት ሕጋዊነትና ሰብአዊነት ለጎደላቸው ለእነዚህ አሰቃቂ ድርጊቶች፣ ስያሜ መስጠትም ሆነ መግለጽ ከባድ ነው።

ሃይ ባይ በሌለበት፣ በጥቂት ቡድኖችና ግለሰቦች አማካኝነት አኢህ ወአክበር! በማለት በምእመናን ላይ የተፈጸመውን ይህን ተግባር ጥቃቱ በተፈጸመባቸው አካባቢዎች ያሉ የእስልምና አባቶችና እናቶች ያወገዙት ሲሆን፤ መንግሥትም በጥቃት ፈጻሚዎቹና ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ የአመራር አካላትና

አባላት ላይ ርምጃ ለመውሰድ በማጣራት ላይ የሚገኝበት ሁኔታ፣ ችግሩ በሕግ የተፈቀደ እስከሚመስል ዝም ተብሎ ከታየና ከቆየ በኋላ ቢሆንም፣ በአሁኑ ሰዓት ያለው የክትትል ሁኔታ የሚበረታታ ነው። ጥፋት ፈጻሚ የሆኑት ጥቂት ቡድኖች፣ የወንጀል ድርጊታቸውን ሲፈጽሙ፣ በተወሰነ ደረጃ ከአንዳንድ የእስልምና አማኞችና አዛውንት ከሆኑ አባቶች ሰብአዊ ተግባር ውጪ፣ ለተወሰኑ ሰዓታት የገደባቸውና የተከላከላቸው የማኅበረሰብም ሆነ የመንግሥት ኃይል አልነበረም። ስለዚህ ድርጊቱ ሃይማኖትና ዘርን ሳይለይ ሁሉንም ያሳዘነ ከመሆኑ አንፃር፣ የጥፋት ዘመቻው ይህን ያህል ጉዳት በታቀደና በተደራጀ ሁኔታ አንድ ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ማድረስ ስለቻለበት ዓላማ፣ ግብ፣ ዐቅም፣ ዝግጅትና ምቹ ሁኔታ ጭምር እንጂ፣ የጥፋቱ መገለጫና ውጤት የሆነውን የሕመም ስሜት(ጉዳት) በማከም ላይ ብቻ የተገደበ እንዳይሆን መታየት አለበት።

ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን፡- የሀገራቸው ሰላም መሆን የሚገዳቸውና የሚያስጨንቃቸው፣ እንደማንኛውም ዜጋ ለልማቷና ለልዕልናዋ አስተዋጽኦ ማድረግ፣ እንዳስፈላጊነቱም ሰማዕትነት መክፈል የሚጠበቅባቸው እና ሀገራቸው ያለችበትን ሁኔታም የሚረዱ መሆኑ አያጠያይቅም። ይሁን እንጂ የሀገሪቱን ሰላም መሆን የማይፈልጉ ቡድኖች በአሁኑ ሰዓት ከሌላው ነጥለው ኦርቶዶክሳውያንን በተለየና ተደጋጋሚነት ባለው መንገድ እያጠቁ ያሉበትን ሁኔታ በአግባቡ አለመገንዘብ፤ ጥቃቱ በማንኛውም ዜጋ ላይ እየተፈጸመ ያለ ነው ማለትና ተራና ቀላል አድርጎ መመልከት፤ እንዲሁም በቀጣይ የሚመጣው ችግር ማን ላይና ምን ሊሆን ይችላል? ብሎ አለማሰብና አለመዘጋጀት፤ ሞኝነት ነው።

ስለሆነም የጥፋት ተልእኮ ባነገቡ ጥቂት ቡድኖችና ግለሰቦች፣ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሕይወት፣ ሥነ አእምሮ፣ አካልና ንብረት ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት በምንም መልኩ ሙሉ ለሙሉ መካስ የማይቻል ቢሆንም፤ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ወደነበሩበት ለመመለስ፣ በሁሉም በኩል ጥረት ማድረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በተደጋጋሚነት እየተከሠተ ያለውን ይህን ጥፋትና ችግር ለማስቆም፡- ሁላችንም የጥፋት ድርጊቱን ዓላማ፣ ግብና ዕቅድ መገንዘብ፣ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው። በዚህ መሠረት ፖለቲካን ሽፋን በማድረግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን፣ እንደ ፋሲካ በግ ለእርድ በሚቀርቡበት ሴራ፣ ውስጥ፣ በቅርብም ሆነ በሩቅ እየተሳተፉ ያሉ አካላት እነማን እንደሆኑ በመለየት፣ የጥፋት ተልእኮውና ሴራው ዘላቂነት ባለው መንገድ እንዲቆም፣ ትኩረት ሰጥተን በየድርሻችን ለመሥራት ጥረት ማድረግ ይኖርብናል።

ከተፈጸሙት የጥፋት ድርጊቶች በኋላ ሁኔታውን ያወገዙ አካላት ይህን ክፉ ድርጊት ከማውገዝ ባለፈ፣ ከጥፋት ድርጊቱ በስተጀርባ ያለውን ድብቅ ሴራ ፈልፍሎ በማውጣት ጥፋተኞችን ለሕግ ማጋለጥ ከዚህ በተጨማሪም ካለፈው ማለትም ማድረግ ይገባቸው ከነበረውና ካልነበረው ተምረው፣ የሚመጣውን ጊዜ በመዋጀት፣ በየድርሻቸው ዘላቂ መፍትሔ ሊያስገኙ የሚችሉ ሥራዎችን መሥራት ይገባቸዋል።

ባጠቃላይ ችግሩ በመወገዝ ብቻ ያልቆመና ላለፈው ብንዘገይም የሚመጣውን ለመቅደም ማሰብ ያለብን ስለሆነ፣ ዘላቂነት ያለው መፍትሔ ለመስጠት፡- በጉዳዩ ላይ ቀጣይ ሥራዎችን (ክትትሎችን፣ ጥናትና ምርምሮችን እንዲሁም ውይይትና ምክክሮችን) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በየጊዜው ውይይት ማድረግ ወሳኝነት አለው። በሌላ በኩል ደግሞ ጥፋቶችና ችግሮች የሚወገዱት በሚገባው ደረጃ አውጥተን ስንነጋገርባቸው እንጂ ስንሸፋፍናቸው አይደለም። ስለሆነም በጉዳዩ ላይ ዘላቂነትና ተጨባጭነት ያላቸውን ሥራዎች በየድርሻችን እየሠራን፣አፈጻጸማቸውንም በየጊዜው በመገምገም፣ ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን ብሎም ሀገርን ከአጥፊዎች እንጠብቅ። አጥፊዎችም ርምጃ እንዲወሰድባቸውና ከዚህ መሰል ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት አለበት በማለት ማኅበሩ መልእክቱን ያስተላልፋል።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# ሱባኤ



*አባ ፍቅረማርያም መኩሪያ*

ሱባኤ ቃሉ የግእዝ ሲሆን ሰባት ቁጥር ማለት ነው። ሰባት ቁጥር ደግሞ በዕብራውያን አቆጣጠር ፍጹም ቁጥር ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ በሰባት በሰባት የተጠቀሱ ነገሮችን ተጽፈው እናገኛለን። ለምሳሌ፡- አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን በስድስት ቀን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፎአል (ዘፍ.፪፥፪)። ሰው ማለትም ሕያውነት፣ ለባዊነት ነባቢነት እና አራቱ ባሕርያተ ነፍስ ማለትም ነፋስ፣ እሳት፣ ውኃ፣ መሬት የተስማሙለት ማለት ነው። ሌላም በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹ጥበብ ቤትን ሰራች ሰባት ምሶሰዎቿን አቆመች›› (ምሳ.፱፥፩) በማለት ተናግሯል። ጥበብ የተባለው ወልደ እግዚአብሔር ነው። ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በቅዳሴው ‹‹ጥበብሰ መድኃኒነ ውእቱ፤ ጥበብ ግን መድኃኒታችን ነው›› እንዲል። ቤት የተባለች ቤተ ክርስቲያን ናት ሰባት ምሰሶዎች ተብለው የተነገሩት በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ናቸው። ይህ ብቻ አይደለም የሰባትን ፍጹምነት የሚያስረዱ ሌሎችም አሉ። ሰባቱ የጸሎት ጊዜያት "ስለ እውነት ፍርድህ በቀን ሰባት ጊዜ አመሰግንሃለሁ።" (መዝ.፻፲፰፥፻፷፬) ሰባቱ ሊቃነ መላእክት (ራእ. ፰፥፪) በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት ተመለከትኩ እንዲል። እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው የሰባት ቁጥርን ፍጹምነት የሚያስረዱ ለምሳሌነት የተጠቀሱ ናቸው።

ሌላው ሱባኤ ማለት በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በምጽዋት፣ ወዘተ… ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በቁርጥ ኅሊና፣ በተዘጋጀ ልቡና፣ በቤት፣ በገዳም ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ነው። ሰባቱን ዕለታት አንድ እያለ በመቍጠር ሰው እንደ ፍላጐቱ አንድ ሱባኤ ሰባት ቀን፣ ሁለት ሱባኤ ዐሥራ አራት ቀን፣ ሦስት ሲባኤ ሃያ አንድ ቀን… እግዚአብሔርን ደጅ ለመጽናት በጾም፣ በጸሎትና በስግደት ሳምንቱን በመንፈሳዊ ትሩፋት የሚጠመድበት ማለት ነው።

## ሱባኤ በስንት ይከፈላል?

ሱባኤ በሦስት ይከፈላል እነርሱም ፩ የግል፣ ፪.የማኅበር፣ ፫.የአዋጅ በመባል ይታወቃሉ። ከዚህ በታች በጥቂቱ ለመመልከት እንሞክራለን፡-

### ሀ/ የግል ሱባኤ፡-

ይህ በግል የሚደረገው ሱባኤ በምክረ ካህን በፈቃደ እግዚአብሔር የሚከወን ነው ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ኃጢአት ሠርቶ ኃጢአቱን ለመምህረ ንስሓው በተናዘዘ ጊዜ መምህረ ንስሓው የሚሰጠው ቀኖና በሱባኤ ሊወሰን ይችላል ይህንን ሱባኤ በግል ተነሳሒው እና የንስሓ አባቱ ብቻ የሚያውቁት። ሌላው በዚህ በግል ሱባኤ አንዳንድ በገዳም ያሉ አባቶችና እናቶች እንዲሁም የበረቱ አንዳንድ ምእመናን በተለያዩ የአጽዋማት ጊዜ በግላቸው ከሰው ተለይተው በቦታ ተወስነው ዋሻ ወይም ቤት ዘግተው በጾም፣ በጸሎት በስግደትና በአርምሞ የሚያሳልፉ አሉ። ይህም የሚቻል እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌል ‹‹አንተ ግን ስትጸልይ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል›› (ማቴ.፮፥፮) በማለት እንደተናገረ።

### ለ/ የማኅበር ሱባኤ፡-

ይህ ሱባኤ በተለይ በገዳማት የሚኖሩ አባቶች መነኮሳትና እናቶች መነኮሳይያት የሚጠቀሙበት የሱባኤ ዓይነት ነው። ይኸውም በሚኖሩበት ገዳም የተነሣ ፈተና ካለ ያንን ልዑል እግዚአብሔር እንዲያርቅላቸው ገዳማቸውንም እንዲጠብቅላቸው በማኅበሩ አበምኔት ወይንም እመ ምኔት በመታዘዝ የማኅበር ሱባኤ በኅብረት በመሆን በጾም፣

በጸሎትና በስግደት ሊገቡ ይችላሉ:: ቅዱስ ዳዊት ‹‹ ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው እነሆም ያማረ ነው›› (መዝ. ፻፴፪፥፩) ብሎ እንደተናገረ ገደማውያኑ የያዙትን ሱባኤ ተቀብሎ እግዚአብሔር ገዳምን ይጠብቃል:: የመጣውን ፈተና ይመልሰዋል:: መነኮሳትና መነኮሳይያት ስለ ገዳማቸው ብቻ ያይደለ ስለ ሀገርም ስለ ቤተ ክርስቲያንም ስለ ሕዝቡም መጠበቅ ጭምር ሱባኤ ሰለሚይዙ በእነርሱ ልመና ልዑል እግዚአብሔር ይጠብቀናል:: የማኅበር ሱባኤ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የሆኑት ቅዱሳን ሐዋርያት ናቸው:: የሐዋርያትን ሥራ የጻፈልን ቅዱስ ሉቃስ የሐዋርያትን ስም ይዘረዝርና ‹‹እነዚህ ሁሉ ከሴቶች እና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር›› (ሐዋ.፩፥፲፬-፲፭) ይላል:: ሐዋርያት ድንግል ማርያምን በመካከል አድርገው ይዘውት የነበረው ሱባኤ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ጌታ በዐረገ በዐሥረኛው ቀን ከሞት በተነሣ በሃምሣኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ ወርዶላቸው በአገሩ ሁሉ ቋንቋ ተናግረዋል:: ዙረው ወንጌልን አስተምረዋል:: መከራውን ሁሉ ታግሰው አገልግለዋል፤ በስተመጨረሻም በፍጹም ጽናት በሰማዕትነት አርፈዋል፤ የክብር አክሊል ተሸልመዋል:: ዛሬም በሰማያት ስለ እኛ እየማለዱ አሉ ይሄ ሁሉ ጸጋ እና ክብር የተገኘው በማኅበር ሱባኤ ነው::

## ሐ/ በአዋጅ አጽዋማት የሚያዝ ሱባኤ፡-

ይህ ሱባኤ ክርስቲያኑ በሙሉ በአዋጅ አጽዋማት ማለትም በሰባቱ አጽዋማት የሚይዘው ሱባኤ ነው በአዋጅ ጾም ለምሳሌ የነነዌ ሰዎች እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው ወደ እግዚአብሔር በመመለሳቸው ተጠቅመውበታል:: ሊመጣባቸው ከነበረው የእሳት መቃጠል በአዋጅ በያዙት ጾምና ጸሎት (ሱባኤ) በሦስት ቀን ልዑል እግዚአብሔር የምሕረት ፊቱን መልሶላቸው ከመቅሰፍት ድነውበታል:: (ዮና. ፫ እና ፬) እንደዚሁም በአስቴር ዘመን እስራኤላውያን ‹‹ሃማ›› ከተባለ ጠላታቸው እና ከተመከረባቸው ክፉ የመጥፋት ምክር የዳኑት በአዋጅ በያዙት ሱባኤ ነበር::

በመጽሐፈ አስቴር ተመዝግቦ እንደምናገኘው ችግር በመጣ ጊዜ በአዋጅ መጾም መጸለይ (ሱባኤ መግባት) ከመጣ መከራ ያድናል:: ‹‹አስቴርም እንዲህ ብሎ ለመርዶክዮስ እንዲመለሱ አዘዘችው ሄደህ በሱሳ ያሉትን አይሁድ ሁሉ ሰብስብ ለእኔም ጹሙ ሦስት ቀን ሌሊቱን እና ቀኑን አትብሉ፤ አትጠጡም፤ እኔና ደንገጡሮቼም ደግሞ እንዲሁ እንጾማለን ምንም እንኳ ያለ ሕግ ቢሆን ወደ ንጉሡ እገባለሁ፤ ብጠፋም እጠፋለሁ መርዶክዮስም ሂዶ አስቴር እንዳዘዘችው ሁሉ አደገ::›› (አስ.፬፥፲፮) እንዲል:: ይህንንም የእስራኤልን ሱባኤ ተቀብሎ ልዑል እግዚአብሔር ሃማን በራሱ ምክር ባዘጋጀው ግንድ ተሰቅሎ እንዲሞት አድርጐታል:: (አስ. ፯፥፱-፲)

**ሱባኤ ማለት በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በምጽዋት፣ ወዘተ... ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በቁርጥ ኅሊና፣ በተዘጋጀ ልቡና፣ በቤት፣ በገዳም ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ነው።**

## ሱባኤ ለምን እንገባለን?

ሱባኤ የምንገባባቸው ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም ከዚህ በታች ግን ጥቂቶችን እንመለከታልን::

## ፩/ ልዑል እግዚአብሔርን ለመለመን፡-

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌል ለምኑ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያ አንኳኩ ይከፈትላችኋል፡፡ (ማቴ.፯፥፯) ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት ሱባኤ የምንገባው ልዑል እግዚብሔርን ለመለመን ነው፡፡ በልመናችን ጊዜ ግን በማስተዋል መለመን ይገባል፡፡ በቅዱስ ወንጌል የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብ እና ዮሐንስ እንዲሁም እናታቸው ማርያም ባውፍልያ የምትለምኑትን የማታውቁ ተብለዋል፡፡ (ማቴ. ፳፥፩)

## ፪/ ከቅዱሳን በረከት ለመሳተፍ፡-

በረከትን የሚያድል እግዚአብሔር ቢሆንም ቅዱሳን ለእግዚአብሔር ካላቸው ቅርበትና ከተሰጣቸው ቃል ኪዳን የተነሳ በረከትን ከእግዚአብሔ እየለመኑ ያሰጡናል፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ ‹‹በረከት በቅዱሳን ራስ ላይ ነው››(ምሳ. ፲፥፯) ሲል እንደተናገረ የቅዱሳን በረከት ለማግኘት ሱባኤ እንገባለን ለምሳሌ የአቡነ ተክለሃይማኖት ስም የሚጠራበት ገዳም እና ቤተ ክርስቲያን ቢኖር የቅዱሱን በረከት በሱባኤ ማግኘት ይቻላል፡፡ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔርም በነቢዩ በኢሳይየስ አድሮ ‹‹… በቤት እና በቅጥሬ የማይጠፋ ዘለዓለማዊ ስም እሰጣቸዋለሁ›› (ኢሳ.፶፮፥፬) ብሎ እንደነገረን በቅዱሳን መካናት በተለይም ስሙ የሚጠራው ቅዱስ ተጋድሎውን በፈጸሙበት ቃል ኪዳን በተቀበለበት ዐፅሙ ባረፈበት ቦታ የቅዱሳን በረከት ተሳታፊ ለመሆን ሱባኤ ይያዛል፡፡

## ፫/ የተሠወረ ምሥጢር እንዲገለጽ፡-

የተሰወሩ ምሥጢራት እንዲገለጹልን በሱባኤ እግዚአብሔርን መጠየቅ ይገባል፡፡ የግብፅ ንጉሥ ፈርኦን የተሰወረበትን ምሥጢር የእግዚብሔር ሰው ዮሴፍ እንደገለጠለት (ዘፍ.፵፩፥፲፬-፲፮) የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር እና ብልጣሶር የተሰወረባቸውን ምሥጢር ነቢዩ ዳንኤል እንደገለጠላቸው ( ዳን. ፬፥፱፤ ዳን.፭፥፬) እንደዚሁም በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ተቃጥለው የነበሩ መጻሕፍት እንዲገለጡለት ነቢዩ ዕዝራ ሱቱኤል ወደ ልዑል እግዚአብሔር በጸለየው ጸሎት በጾመው ጾም በያዘው ሱባኤ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ኡራኤል ወደ እርሱ መጥቶ ጠፍተው የነበሩትን ፵፮ የኦሪት መጻሕፍት እንደ ገለጠለት እና በስተ መጨረሻም ሞትን እንዳያይ እንዲሰወር አድርጎታል፡፡ (ዕዝ.ሱቱ.፩) እንዲህ ለአብነት ያህል እነዚህን ከላይ የተመለከትናቸውን ጠቀስን እንጂ ብዙ እንቆቅልሻቸው በሱባኤ የተፈታላቸው ቅዱሳን አባቶች እና እናቶች አሉ፡፡ እኛም በሕይወታችን እንቆቅልሽ የሆነብን ነገር ሁሉ እንዲፈታልን እና ለጥያቄያችን መልስ እንድናገኝ በሱባኤ ልዑል እግዚአብሔርን ደጅ መጽናት ይገባል፡፡

# በሱባኤ የተጠቀሙ እነማን ናቸው?

በሱባኤ የተጠቀሙ እጅግ በጣም ብዙ ቢሆኑም በዚህ ጽሑፍ ግን እጅግ ጥቂቶችን ለአብነት ያህል እንመለከታለን፡፡

## ሀ/ አዳም፡-

አባታችን አዳም ከገነት በተሰደደ ጊዜ በበደሉ ምክንያት ገነትን ያህል ቦታ እግዚአብሔርን ያህል ቸር ጌታ በማጣቱ እጅግ አድርጎ አዘነ ስለዚህም ንስሓ ገብቶ ፈጣሪውን በሱባኤ ደጅ ጠና፡፡ ከደሙም ጋር የስንዴ መሥዋዕትን አቀረበ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔርም የዛሬውን ተቀበልኩህ ዓለም የሚድነው በልጄ ደም ነው፡፡ አምስት ቀን ተኩል ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በሜዳህ ድሄ፣ በመስቀል ተሰቅዬ፣ ቤዛ እሆንህለሁ አለው፡፡ አምስት ቀን ተኩል በእግዚአብሔር አቆጣጠር ፭ ሺህ ፭መቶ ዘመን ነው የገባውንም ቃል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው በመሆን ፈጸመለት መ.ቀሌምንጦስ አንቀጽ፡ ፬ (ገላ.፬፥፬) ይህ የሱባኤው ውጤት ነው፡፡

## ለ/ ነቢያት፡-

ቅዱሳን አባቶቻችን ነቢያት የጌታችንን ሰው መሆን እየናፈቁ በብዙ ሱባኤ ደጅ ይጠኑ ነበር፡፡ ለምሳሌ ሙሴ፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ እና ዳዊት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በተለይ ቅዱስ ዳዊት ‹‹በእውነት ወደ ቤቴ አልገባም ወደ ምንጣፌ አልጋም አልወጣም ለዐይኖቼ መኝታ ለሽፋሽፍቶቼ እንቀልፍ ለጉንጮቼም እረፍት አልሰጥም ለእግዚአብሔር ሥፍራ ለያዕቆብ አምላክ ማደሪያ እስካገኝ›› (መዝ.፻፴፩፥፫)

ብሎ ጽኑዕ ምኞቱን ገልጾአል፡፡ ይህ በጊዜው ዳዊት ለእግዚአብሔር ታቦት ቤተ መቅደስ ለመሥራት ማደሪያውን ለማዘጋጀት የያዘውን ሱባኤ ያመለክታል፡፡ ምሥጢሩ ግን የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔር ማደሪያው የምትሆን ድንግል ማርያምን ለማየት አምላክ ሰው የሚሆንበትን ጊዜ የመናፈቅ ነው፡፡ ስለሆነም ሱባኤውን የተቀበለለት አምላክ መልስ ሲሰጠው ‹‹እነሆ በኤፍራታ ሰማነው በዱር ውስጥም አገኘነው›› (መዝ.፻፴፩፥፮) ብሎ ጌታ በኤፍራታ ቤተ ልሔም የሚወለድ መሆኑን በግዕዝ ሕፃናት ሲያለቅስ እንደሰማው ሁኖ በትንቢት መነፅር ተመለከተው፡፡ ይህ ሁሉ የሱባኤ ውጤት ነው፡፡

## ሐ/ ሐዋርያት፡-

ክቡራን አባቶቻችን ሐዋርያት በሱባኤ ተጠቅመዋል የተሰወረው ምሥጢር ተገልጾላቸዋል፡፡ በተለይ የአባቶቻችን የሐዋርያት ሱባኤ የሚጠቀሰው በድንግል ማርያም ምክንያት የገቡት ሱባኤና ያገኙት ውጤት ነው፡፡ ይኸውም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዚህ ዓለም ፷፬ ዓመት በንጽሕና፤ በቅድስናና በድንግልና ኑራ ጥር ፳፩ ቀን ከዚህ ዓለም ድካም ባረፈች ጊዜ ማለትም ነፍሷ ከሥጋዋ በተለየች (በሞተች) ጊዜ አክብረው ገንዘው እያመሰገኑ ወደ ጌቴ ሴማኒ ለመቅበር ሲወስዷት አይሁድ የእመቤታችንን ሥጋዋን በእሳት ለማቃጠል መጡ፡፡ ከእነሱ መካከል ታውፋንያ የተባለው ደፋር የድንግል ማርያምን ሥጋዋን ወደ መሬት ለመጣል በቀረበ ጊዜ የአልጋውንም ሸንኮር በእጅ በያዘ ጊዜ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ እጆቹን በእሳት ሰይፍ ቆረጣቸው፡፡ ያን ጊዜ ወደ ልቡ ተመልሶ ይቅርታ ጠየቀ፤ ድንግል ማርያምም በኀቡዕ ተአምር ቅዱስ ጴጥሮስን አዝዛ የተቆረጠ እጆቹን መለሰችለት፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም ለታውፋንያ በትር ሰጥቶ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የድንግል ማርያምን አማላጅነት እንዲመሰክር አዘዘው፡፡ እርሱም በአይሁድ መካከል መስክሮ በድንጋይ ተወግሮ በሰማዕትነት አረፈ፡፡ (ምንጭ)

የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል የድንግል ማርያምን ሥጋ ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር ወደ ሰማይ አሳረገ፡፡ ሥጋዋንም በዕፀ ሕይወት ሥር አኖረው መላእክትም ሥጋዋን ያጥኑ ነበር፡፡ ነፍሷ ግን በልጇ ቀኝ በክብር ተቀመጠ (መዝ.፵፬፥፱) ወንጌላዊ ዮሐንስም ይህን አይቶ ተመልሶ መጥቶ ለሐዋርያት ነገራቸው እነርሱም ዮሐንስ እንዳየ ስላላዩ እንደሰማ ስላልሰሙ የድንግል ማርይምን ሥጋ ለማግኘት ከነሐሴ ፩-፲፬ ቀን ሁለት ሱባኤ ከጾሙ ከጸለዩ በኋላ ጌታ የእመቤታችንን ሥጋ አምጥቶ ሰጣቸው፡፡ እነርሱም ወስደው በጌቴ ሴማኒ ቀበሯት፡፡ በልጇ ሥልጣን ተነሥታ በዕዝራ መሰንቆ በዳዊት በገና በመላእክት እልልታ ስታርግ ቶማስ በደመና ሲመጣ ተመለከታት፡፡ እጅግ አዝኖ ከደመናው ሊወድቅ ወደደ ቀድሞ የልጅሽን ትንሣኤ አላየሁ አሁን ደግሞ ያንችን ብሎ እመቤታችንም አጽናንታ “ከአንተ በቀር ትንሣኤዬንም ዕርገቴንም ያየ የለም” ብላ ለበረከት እንዲሆናቸው ሰበኗን ሰጠችው፡፡ እርሱም ከእርሷ ተባርኮ ወደ ሐዋርያት መጣ፡፡

ሐዋርያቱም ተሰብስበው አገኛቸው የእመቤታችን ነገር እንዴት ሆነ? ብሎ ጠየቃቸው እነርሱም ሥጋዋን አግኝተን ወስደን ቀብርናት አሉት፡፡ እርሱም ‹‹ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር›› እንዴት ይሆናል? አላምንም አላቸው፡፡

ቅዱስ ጴጥሮስ ቀድሞም ተጠራጣሪ ነህና ተነሥ እናሳይህ ተጠራጥረህ ስታጠራጥር እንዳትኖር ብሎ ወደ ጌቴ ሴማኒ መቃብር ወስዶ መቃብሩን ቢከፍት የድንግልን ሥጋ አጣው፡፡ ቶማስም እመቤታችን ከሞት ተነሥታ ዐርጋለች፡፡ ይህው ሰብኗ ብሎ ለበረከት ሰጣቸው፡፡ ያንን ተከፋፍለው በዚያ ተአምራት ሲያደርጉበት ከኖሩ በኋላ ቶማስ ትንሣኤሽን ዕርገትሽን አይቶ እኛ እንዴት ይቀርብናል ብለው በዓመቱ ነሐሴ ፩ ጾም ጀመሩ ነሐሴ ፲፮ ቀን ሐዋርያትን ሁሉ ጌታ ወደ ሰማይ አውጥቷቸው የእመቤታችንን ትንሣኤዋን እና ዕርገቷን አሳያቸው፡፡ እርሷንም መንበር አድርጐ ቀድሶ ሥጋውን ደሙን አቀበላቸው፡፡ ለእመቤታችንም የከበረ ቃል ኪዳን ከሰጣት በኋላ የእመቤታችን ትንሣኤዋን እና ዕርገቷን እንዲያስተምሩ ተዝካሯን እንዲያደርጉ ሐዋርያትን አዘዛቸው፡፡ እነርሱም የታዘዙትን ፈጸሙ፡፡

ይህ ከላይ የተመለከትነው ፍጹም የሆነ ሱባኤ የሚያስገኘውን ውጤት ነው፡፡ እኛም በሕይወታችን ሰለሚያስፈልገን ነገር ሃይማኖት ለማጽናት ምግባር ስለ ማቅናት በምንይዘው ሱባኤ መልስ እንድናገኝ የልዑል እግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነት የጻድቃን የሰማዕታት የቅዱሳን ሁሉ ጸሎት ሁላችንን ይርዳን አሜን፡፡

## “ተለዐለት እምድር በስብሐት ውስተ ሰማያት ወበህየ ነበረት፤ በክብር በምስጋና ከምድር ወደሰማይ አረገች በዚያም ተቀመጠች”

*(ቅዱስ ያሬድ)*

# ትምህርተ ሃይማኖት

*በመጋቤ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ ማናዬ*

በቅድሚያ ለሁላችሁም ሰላመ እግዚአብሔር ይድረሳችሁ! ሞት በነገሠበት ቸነፈር ጥላውን በጣለበት ዓለም ውስጥ በሕይወት ጠብቆ በሀብት ስቦ በረድኤት አቅርቦ ለእመቤታችን የትንሣኤ እና የዕርገት በዓል በሰላም ስላደረሰን ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን!

ከነሐሴ ፩-፲፮ ጾመ ፍልሰታን ጾመን በነሐሴ ፲፮ የምናከብረው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የዕርገት በዓል ነው። ለጾሙ ምክንያት የሆኑት የእመቤታችን እረፍት፣ ትንሣኤ እና ዕርገት ናቸው። ጾሙን የጾሙት ቅዱሳን ሐዋርያት ሲሆኑ የጾሙበት ምክንያት የእመቤታችን ጉዳይ እረፍት፣ ፍልሰት፣ ዕርገት ስለ ሆነ ጾመ ፍልሰታ ለማርያም በሚል ስያሜ ይጠራል። በተጨማሪም በጸዋሚዎች ጾመ ሐዋርያትም ይባላል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አክብራ ከተቀበለቻቸው ሰባት አጽዋማት ሰፍራ ቆጥራ ለምእመናን አስተምራ ከምትጾማቸው አንዱ ጾመ ፍልሰታ ለማርያም የሚባለው ጾም ሲሆን ጾሙ ከሊቅ እስከ ደቂቅ በልዩ ፍቅር የሚወደድ ጾም ነው።

ከስያሜው ስንነሣ ጾም እና ፍልሰት የሚሉ ሁለት ቃላትን አጣምሮ ጾሙን እና የጾሙን ምክንያት አስተባብሮ የሚገልጥ ነው። አሁን የምንመለከተው ጾም የሚለውን ሳይሆን ለጾሙ መነሻ የሆነውን የእመቤታችንን ዕርገት ነው። ይህን የእመቤታችንን የእረፍት፣የትንሣኤ እና የዕርገት በዓል ስናስብ በእግረ ኅሊና ወደ ኋላ ተመልሰን ወደ ፵፱ ዓመተ ምሕረት እንጓዛለን። እመቤታችን ያረፈቸው በ፵፱ ዓ.ም ጥር ሃያ አንድ ቀን ሲሆን የተነሣችው እና ያረገችውም በዚያው ዓመት ነሐሴ ወር አሁን ፍልሰታ ለማርያም ብለን በምናከብረው ወቅት ነው። ይህም ማለት የዛሬ ፲፱፻፸፫ ዓመት በዘመነ ማቴዎስ የተከናወነ ነው። ፍልሰታ የሚለው የግእዝ ቃል ፈለሰ ተሰደደ ከሚል ግሥ የወጣ ቃል ነው ዐውዳዊ ፍችውን ስንመለከት እንደየአገባቡ ልዩ ልዩ ትርጉም ይሰጣል። መፍለስ፣ መሰደድ፣ መለየት፣ ቦታን መልቀቅ፣ መሰወር፣ ከሰው ርቆ መኖር፣ እርገት ወዘተ ••• ተብሎ ይተረጎማል።

ፍልሰታ ለማርያም ሲባል የእመቤታችንን ከዚህ ዓለም በሞት መለየትን በትንሣኤ ከመቃብር መውጣትን በዕርገት ከምድር ወደሰማይ ማረግን የሚገልጽ ቃል ነው። እመቤታችን በዚህ ዓለም ስድሳ አራት ዓመታትን ኖራለች። በእርግጥ የዚህ ዓለም ኑሮ መኖር አይባልም መኖር ከሚለው መቆየት የሚለው ይስማማዋል መቆየት ጊዜያዊነትን ሲያሳይ መኖር የሚለው ደግሞ። ዘለዓለማዊነትን ገላጭ ነው።

የዚህ ዓለም ቆይታዋ በንጽሕና በቅድስና ያጌጠ ንጽሕናን ቅድስናን ለዓለም የገለጠ ክብሯም ከፍጡራን የበለጠ እና ለማንም ያልተሰጠ ነው።

በዚህች ምድር ላይ “ቀደስኩከ እምከርሰ እምከ፤ በእናትህ ሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፤ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ” (ኤር.፩፥፭) ከተባለ ከኤርምያስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ በኤልያስ ግብር ጸንቶ ይኖራል ከተባለለት ከዮሐንስ መጥምቅና ከሌሎችም በቅድስና ከኖሩ በንጽሕና ከከበሩ ቅዱሳን በተለየ ቅዱስ ሕይወት የነበረች፣ያለችና የምትኖር ናት። ልዩ የሚያደርጋትም ክብሯና ቅድስናዋ እንደ ሌሎች ቅዱሳን ጤዛ ልሶ ደንጊያ ተንተርሶ ድምፀ አራዊትን ግርማ ሌሊትን ታግሶ እንደ ሰማዕታት ከነደደ እሳት ገብቶ አንገትን ለሰይፍ ሰለት፣ ሰውነትን ለእሳት ሰጥቶ በገድል የተገኘ አይደለም። የእግዚአብሔር እናት ለመሆን ሰው ሊያውቀው አእምሮ ሊያራቅቀው በማይችል ድንቅ የእግዚአብሔር ጥበብ በመመረጥ የተገኘ እንጂ። የእመቤታችን ክብሯ ልዩ ነው ከሰማያውያን መላእክት ከምድራውያን ደቂቀ አዳም ይልቅ እጅግ የተለየች እና የተመረጠች ናትና። ክብሯ ልዩ ነው

የመመረጧ ግብርም ድንቅ ነው። የሔዋን ልጆቿ በቁጥር እጅግ ብዙ ናቸው መርገሟን ማስወገድ ዕዳ በደሏን ማሰረዝ የቻለች የሔዋን ዕዳ ከፋይ የሆነች ግን እመቤታችን ብቻ ናት።

ጥበበኛው ሰሎሞን በመኃልዩ ይህን ሲያስረዳ "ርግቤ መደምደሚያዬም አንዲት ናት፤ ለእናትዋ አንዲት ናት ለወለደቻትም የተመረጠች ናት። ቈነጃጅትም አይተው አሞገሱአት፥ ንግሥታትና ቍባቶችም አመሰገኑአት።" እንዲል (መኃ. ፮፥፱) የሔዋን ጆሮ ምክረ ከይሲን ሰምቶ ከእግዚአብሔር ጋር መጣላትን አመጣ የሰው ልጆችን ከገነት አስወጣ እግዚአብሔርን ያህል ጌታ፣ ገነትን ያህል ቦታ፣ ልጅነትን ያህል ክብር ገነት መንግሥተ ሰማያትን ያህል ሀገር አሳጣ ይህ ሁሉ የሆነው በሄዋን ምክንያት ነበር። ይህ የተገለበጠው ደግሞ በቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም ነው። ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሃይማኖተ አበው ይህን ሲገልጽ "ነገር ግን ሔዋንን ዲያብሎስ አሳታት የሞት ምክንያት የሚሆን ቃየልን ወለደች ማርያም ግን መልአክ ባበሠራት ጊዜ ሁሉን ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚመራ አካላዊ ቃልን በሥጋ ወለደች። የሔዋን ልብላ ልብላ ማለቷ ዕፀ በለስ የሞት ምክንያት እንደሆነ አስረዳ በዚያም ዕፅ አዳም ተድላ ደስታ ካለበት ከገነት ወጣ ከድንግል የተወለደ አካላዊ ቃል ግን መስቀል የድኅነት ምክንያት እንደሆነ ገለጠ በዚያም መስቀል ቀማኛ ወንበዴ የነበረው ሰው ከአባቱ ከአዳምና ከቀደሙ አባቶች ሁሉ ጋር ተድላ ደስታ ወዳለበት ገነት ገባ" (ሃ.አበ. ፷፯፥፬-፸) በማለት አስረድቷል።

ይህም የሚያስረዳን የሔዋን ዕዳ በደል የተወገደው በእናታችን በቅድስት ድንግል ማርያም አማካኝነት ነው። ዓለም በሔዋን ምክንያት ከገነት ሲሰደድ በድንግል ማርያም አማካኝነትም ወደ ገነት ተመልሷል። ሊቃውንቱ መልክአ ውዳሴ በተባለ ድርሰት "ለሔዋን እምነ ከይሲ ዘአስሐታ እግዚአብሔር ናዘዛ ኪያኪ በወሊዶታ፤ ከይሲ ያሳታት እናታችን ሔዋንን አንቺን በመውለዷ እግዚአብሔር አረጋጋት" በማለት የሔዋን ኃዘን የተወገደው፣ ሔዋን ከሞት ወደ ሕይወት ከሲኦል ወደገነት የተመለሰችው ድንግል ማርያምን ያመሰግናሉ።

በቅዱስ መጽሐፍ "አዳምም ለሚስቱ ሔዋን" ብሎ ስም አወጣ። የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና። እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸውም። እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፥ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፥ ለዘለዓለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ከዔደን ገነት አስወጣው፥ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ። አዳምንም አስወጣው፥ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔደን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ።" ዘፍ ፫÷፳-፳፬ ተብሎ የተገለጽውን ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም "በእንተ ሔዋን ተዐፅወ ኆኅተ ገነት ወበእንተ ማርያም ድንግል ተርኅወ ለነ ዳግመ-በሔዋን ምክንያት የገነት ደጅ ተዘጋብን ዳግመኛ በድንግል ማርያም ተከፈተልን" በማለት በውዳሴ ማርያም ድርሰቱ እንደገለጸው የሰው ልጆች ጥያቄ መልስ ያገኘው በእመቤታችን ነው። ዳግማይ አዳም ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር አካላዊ ቃልን ወልዳልናለችና።

**እመቤታችን በዚህ ዓለም ስድሳ አራት ዓመታትን ኖራለች። በእርግጥ የዚህ ዓለም ኑሮ መኖር አይባልም መኖር ከሚለው መቆየት የሚለው ይስማማዋል መቆየት ጊዜያዊነትን ሲያሳይ መኖር የሚለው ደግሞ። ዘለዓለማዊነትን ገላጭ ነው።**

ከሔዋን በተለየ ግብር ጸንታ ከሔዋን የተገኘች ስትሆን ከሔዋን ተለይታ ለሰው ልጆች ሕይወትን የሚሰጠውን ወለደችልን። በዚህ ልዩ ምሥጢር እግዚአብሔር ከእርሷ ተወልዶ ተገለጠ ሞት በሕይወት ተለወጠ። ለዘመናት በሰው ልጆች ላይ ሠልጥኖ የነበረው ዲያብሎስ ደነገጠ ሞት የሰውን ልጅ ገድሎ ወደ መቃብር ይሸኘዋል። በዚህም መንገድ ሥጋ በመቃብር ሲፈርስ ሲበሰብስ ነፍስም በፍዳ ተይዛ በሲኦል ተግዛ ትኖር ነበር ከእርሷ የተወለደው አምላክ ወልደ አምላክ በሞቱ ሞተ ነፍስን ደመሰሰልን የሞተ ነፍስ መነሻ የመከራ ነፍስ መገስገሻ የነበረውን ሞተ ሥጋን የትንሣኤ እና የዕርገት መናገሻ አደረገልን። አስደንጋጭ የነበረው ሞት የሕይወት መንገድ መሆኑ በክርስቶስ ሞት ተገለጠ። በትንሣኤውና በዕርገቱ ይበልጥ ተረጋገጠ። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያስረዳ "ከእኛ አንድ ስንኳ ለራሱ የሚኖር የለምና፥ ለራሱም የሚሞት የለም፤ በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና፥ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን። እንግዲህ በሕይወት ሆነን ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን። ስለዚህ ነገር ሙታንንም ሕያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአልና ሕያውም ሆኖአልና።" (ሮሜ ፲፬ ፥፯-፱) በማለት ገልጾአል።

እመቤታችንም የሞተችው ሞት ይህን መሰል ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር የናፈቁት ሞት ነው። ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ የነበሩ አበው ከሞቱት ሞት ይለያል። ያኛው ፍዳን ያስከትላል ይህኛው ግን ሕይወትን የሚያስከትል ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የሚያኖር ነውና። እመቤታችንም ደግሞ ከሁሉም ቅዱሳን ይልቅ በሕይወተ ሥጋ ቅድመ ፀኒስ እግዚአብሔር በረድኤት ያልተለያት ጊዜ ፀኒስ ድኅረ ፀኒስ እግዚአብሔር በኩነት ማለት ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆኖ አብሯት የኖረ ከቤተ ልሔም እስከ ቀራንዮ ከመካነ ልደቱ እስከ መካነ ሞቱ ያልተለየችው እግዚአብሔርም ያልተለያት ከፅንስቱ እስከ እርገቱ ለኅሊናችን እሩቅ ለልቡናችን ረቂቅ የሆነውን ምሥጢር ተሸከማ ልዩ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆና የኖረች ናት።

እርሷ የሞተችው ሞት ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር መሆኑ ግልጥ ነው። ይህንን ነው ፍልሰታ ለማርያም የምንለው ከዚህ ዓለም በሞት ከመቃብር በትንሣኤ ከትንሣኤ ቀጥሎ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን ሕይወት ለመኖር መለየት፣ መሰደድ፣ መፍለስ፣ መራቅ፣ መሰወር፣ ዕርገት ነው ፍልሰታ ማለት። ከላይ የጽሑፋችን መነሻ ያደረግነው የቅዱስ ያሬድ ዝማሬ ይህን የሚገልጥ ስለ እመቤታችን ዕርገት የሚያስረዳ ነው። "ተለዐለት እምድር በስብሐት ውስተ ሰማያት ወበህየ ነበረት ዘምስለ ወልዳ በየማነ አብ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ከምድር በክብር በምስጋና ወደሰማያት ከፍ አለች( ዐረገች) አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በሚሰጡት ክብር ከልጇ ጋር በዚያ ተቀመጠች" በማለት የእመቤታችን ዕርገቷን የገለጠበት ምስጋና ምስክርነትም ነው። "ተለዐለ" የሚለው ግስ ከፍ ማለትን ወደ ላይ ወደ ሰማይ መውጣትን ማረግን የሚገልጥ ግሥ ነው ይህ ግሥ ለጌታችን ዕርገት መነገሩን ልብ ይሏል "ወዘንተ እንዘ ይብሎሙ ተለዐለ ወነስአቶ ደመና ወዐርገ ሰማየ፤ ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው።" (ሐዋ. ፩፥፱)

በዚህ አንጻር "ተለዐለት" ማለት ዐርገት ማለት መሆኑን እናስተውል። የእመቤታችን ትንሣኤ እና ዕርገት ከቅዱሳት መጻሕፍት የምናገኘው ነው እንጂ ልብ የወለደው አእምሮ የፈጠረው አይደለም። አስቀድሞ በነቢያት የተነገረ ነው እንጂ እንዲህ ተብሎ "አቤቱ፥ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ፥ አንተና የመቅደስህ ታቦት።" (መዝ. ፻፴፩፥፰) አቤቱ ተነሥ የሚለው የጌታችን ትንሣኤ ገላጭ ሲሆን የመቅደስህ ታቦት የተባለችው ቅድስት ድንግል ማርያም ናት።

መቅደስ የተባለ ሰውነቱ ነው። ይህም በቅዱስ ወንጌል "ንሥተዎ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ ወበሠለስ ዕለት አነሥኦ ወውእቱሰ ይቤሎሙ በእንተ ቤተ ሥጋሁ፤ ኢየሱስም መልሶ፦ ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው። ... እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር።" (ዮሐ. ፪፥፲፱-፳፩) ተብሎ ተገልጾአል። ስለዚህ አንተ ተነሥ በማለት የትንሣኤያችን በኩር የሆነ የጌታችንን ትንሣኤ ትእዛዛዊ በሆነ እንደማይቀር በሚያስረግጥ መልኩ የተነገረበት ሲሆን "የመቅደስህ ታቦት" ሰው ሆነህ ያደርክባት የተገለጥክባት እርሷም እመቤታችን ትነሣ በሚል ምልዐተ ንባብ የእመቤታችን ትንሣኤ ትንሣኤ ዘጉባኤን ሳይጠብቅ

ከእርሱ ቀጥሎ የሚፈጸም መሆኑ የተነገረበት ትንቢት እና ምስክርነት ነው፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተነሣች ካልን ዐረገች ማለት ግድ ነው፡፡ ምክንያቱም ትንሣኤ የዕርገት ዋዜማ ነውና፡፡ እመቤታችን በጥር ፳፩ አረፈች፤ በነሐሴ ፲፬ ተቀበረች፤ ዕለቱን በነሐሴ ፲፬ ተነሣች፤ በነሐሴ ፲፬ በዕለተ እሑድ ዐረገች፡፡ ከመ ትንሣኤ ወልዳ እንደ ልጇ ፍጹም ትንሣኤ ተነሣች ከመ ትንሣኤ ወልዳ ማለት ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊትን አያመለክትም ዕለተ እሑድ መሆኑንና የትንሣኤዋን ፍጹምነት ዳግም ሞት የሌለበት ትንሣኤ መነሣቷን እንጂ፡፡ ያን ጊዜ ዕርገቷን ያየ ቶማስ ብቻ ነበር ሌሎች ሐዋርያት አላዩም ነበርና በነሐሴ አስራ ስድስት በዓመቱ ጌታችን ለቅዱሳን ሐዋርያት የእመቤታችን ዕርገቷን የገለጠበት ዜና ትንሣኤዋንና ዜና ዕርገቷን እንዲሰብኩ ያዘዘበት “ዘፀውዐ ስመኪ ወዘገብረ ተዝካረኪ እምሕር ለኪ፤ ስምሽን የጠራውን መታሰቢያሽን ያደረገውን እምርልሻለሁ” ብሎ ለእመቤታችን ጽኑእ የሆነ ቃል ኪዳን ገብቶላታል፡፡

እንዲሁም “ዘፀውዐ ስመክሙ ወዘገብረ ተዝካረክሙ እምሕር ለክሙ፤ ስማችሁን የጠራውን መታሰቢያችሁን ያደረገውን እምርላችሁአለሁ” ብሎ ለሐዋርያትም ተናግሮ የማያስቀረውን ጽኑእ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል፡፡ ነሐሴ ዐሥራ አራት ትንሣኤዋ እና ዕርገቷ ሲሆን ዐሥራ ስድስት የትንሣኤዋ እና የዕርገቷ መታሰቢያ በዓል የሚከበርበት፣ ትንሣኤዋንና ዕረገቷን ላላዩ ሐዋርያት ጌችንና መድኃኒታችን ለሐዋርያት የተገለጠበት፣ ቃል ኪዳን የሰጠበትነው፡፡

ዕርገቷም እንደ ትንሣኤዋ ሁሉ በመጻሕፍት የተነገረ ሲጠበቅ የኖረ ነው፡፡ “ወትቀውም ንግሥት በየማንከ በአልባሰ ወርቅ ዑፅፍት ወኁብርት፤ በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች፡፡” (መዝ. ፵፭፥፱) ትቀውም የሚለውን መተርጉማን ትነብር ይሉታል ንግሥት በቀኝህ ትቀመጣለች ማለት ነው፡፡ “ትቀውም፤ ትቆማለች” ማለት ለፍጡራን ሁሉ ይልቁንም በአማላጅነቷ ለሚያምኑ በቃል ኪዳኗ ለሚማፀኑ አማላጅነቷን አስረጂ ነው፡፡ “ትነብር፤ ትቀመጣለች” ማለት ደግሞ ከዚህ ዓለም ድካመ ሥጋ በዕርገት ማረፏን የተሰጣትን ፍጹም ክብር የሚያስረዳ ነው፡፡ መቆም ተልእኮን፣ መቀመጥ ደግሞ ክብርን ገላጭ ነው፡፡ በቀኝህ ትቀመጣለች የሚለው ቅዱስ ያሬድ በዝማሬው ካነሣው ሐሳብ ጋር አንድ ነው፡፡ “ወበህየ ነበረት ዘምስለ ወልዳ፤ ከልጇ ጋር በዚያ ተቀመጠች” ይላል በዚያ ያለው በመንግሥተ ሰማያት ነው እርሷ በወራሽነት ልጇ በምልዓት ይኖሩባታልና ነው፡፡

**ይህ ፍልሰት የሥጋ ብቻ አይደለም ነፍስና ሥጋዋ ተዋሕደው እንደ ልጇ ትንሣኤ እና ዕርገት ነው እንጂ፡፡ በአንቺ ዘንድ የተመሰገኑ የቅዱሳን ሰዎች ዕርገት ለተጀመረበት ለሥጋሽ እርገት ሰላም እላለሁ፡፡ (መልክአ ፍልሰታ) ተብሎ እንደተገለጸው ፍልሰቷ ነፍስና ሥጋዋ ተዋሕዶ ዳግም ትንሣኤን ሳይጠብቅ መንግሠተ ሰማያትን መውረሷን የሚያመለክት ነው፡፡**

የመጀመሪያዋ የገነት ኗሪ ከቀዳማዊው አዳም ጋር ሔዋን ነበረች፡፡ የመንግሥተ ሰማያት ጀማሪ ደግሞ ከዳግማይ አዳም ክርስቶስ ጋር ዳግሚት ሔዋን እመቤታችን ናት፡፡

"ይቤ ቅዱስ ማሪ ኤፍሬም አፈበረከት ወመምህር ሦርያዊ በእንተ እግዝእትነ ማርያም ድንግል ወትረ በኩሉ ጊዜ እምአመ ልደታ እስከ አመ እረፍታ ወፍልሰታ፤ አፈ በረከት የሦርያው መምህር ቅዱስ ኤፍሬም ዘወትር ድንግል ስለሆነች ስለእመቤታችን ከልደቷ እስከእረፍቷ እና ፍልሰቷ በተናገረበት ድርሳኑ እንዲህ አለ::" (ሃ.አበ. ፵፯÷፩)

ይህ ፍልሰት የሥጋ ብቻ አይደለም ነፍስና ሥጋዋ ተዋሕደው እንደ ልጇ ትንሣኤ እና ዕርገት ነው እንጂ:: (ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ምስለ ነፍስኪ ኢመዋቲ በተሰናዕዎ አሐቲ፤ ከማትሞት ነፍስሽ ጋር በአንዲት መስማማት ለተደረገ ለስጋሽ ፍልሰት ሰላም እላለሁ)፤ "ሰላም ለዕርገተ ሥጋኪ ዘተወጥነ ቦቱ:: ዕርገተ ቅዱሳን ሰብእ ዘበኀቤኪ ተአኰቱ፤ በአንቺ ዘንድ የተመሰገኑ የቅዱሳን ሰዎች ዕርገት ለተጀመረበት ለሥጋሽ እርገት ሰላም እላለሁ:: (መልክአ ፍልሰታ) ተብሎ እንደተገለጸው ፍልሰቷ ነፍስና ሥጋዋ ተዋሕዶ ዳግም ትንሣኤን ሳይጠብቅ መንግሠተ ሰማያትን መውረሷን የሚያመለክት ነው::

ከፍጡራን የሞት እና የውርደት ጀማሪ ሔዋን ስትሆን የትንሣኤና የዕርገት ጀማሪ እመቤታችን ናት:: ልጇን መስለን እርሷን ተከትለን ሁላችን እንደምንነሣና እንደምናርግ የታወቀ ነው:: ተስፋ ምናደርገው ትንሣኤ ዘጉባኤ ለሁላችን አለ:: ጸሎታችን የእምነት መግለጫችንም ይህ ነው "የሙታንን መነሣት ተስፋ እናደርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ" ለዘለዓለሙ የሚመጣው ሕይወት በትንሣኤ የምናገኘው በዕርገት የምናረጋግጠው አይደለምን? ይህም አምላካችን የሰጠን የተስፋ ፍጻሜ ነው:: "በአባቴ ቤት ብዙ ማደሪያና ማረፊያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ኖሮ ቦታ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁና እላችሁ ነበር:: ከሄድሁና ቦታ ካዘጋጀሁላችሁም ዳግመኛ እመጣለሁ፤ እናንተ እኔ ባለሁበት ትኖሩ ዘንድ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ::" (ዮሐ. ፲፬÷፪) በማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ጽኑእ ተስፋ ለዘለዓለም የጸና ምእመናንም ይህን ተስፋ ሰንቀው ሃይማኖታቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ነው::

ይህ ለሰው የተሰጠው ተስፋ ማለትም መንግሥተ ሰማያትን ወርሶ መኖር አስቀድሞ የተሰጠው ለእመቤታችን ነው ኋላ ለሁላችን ይሆናል:: "ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን:: ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ::" (፩ኛ ተሰ. ፬ ÷፲፮-፲፰) ተብሎ እንደተነገረው::

ባጠቃላይ "ተለዐለት እምድር በስብሐት ውስተ ሰማያት ወበህየ ነበረት፤ በክብር በምስጋና ከምድር ወደሰማይ ዐረገች በዚያም ተቀመጠች" በማለት ቅዱስ ያሬድ የገለጸው እመቤታችን ድንግል ማርያም እንደልጇ እንደወዳጇ በይባቤ መላእክት በክብር፣ በምስጋና ከሙታን ተለይታ መነሣቷን፣ እንዲሁም ወደሰማይ ማረጓን፣ ከዚህ ዓለም ውጣ ውረድ፣ ድካም፣ እንግልት ማረፏን፣ በክብር መንግሥተ ሰማያትን መውረሷን የሚያስረዳን ነው:: እንደ ልጇ ትንሣኤና ዕርገት የእርሷንም ትንሣኤና ዕርገት በማመን ከትንሣኤዋና ከዕርገቷ በረከትን እንዲያሳትፈን እግዚአብሔር ይፍቀድልን፤ የእመቤታችን ቃል ኪዳን ረድኤት ይደረግልን አሜን !!

**ከፍጡራን የሞት እና የውርደት ጀማሪ ሔዋን ስትሆን የትንሣኤና የዕርገት ጀማሪ እመቤታችን ናት:: ልጇን መስለን እርሷን ተከትለን ሁላችን እንደምንነሣና እንደምናርግ የታወቀ ነው:: ተስፋ ምናደርገው ትንሣኤ ዘጉባኤ ለሁላችን አለ::**

# ክብረ ክህነት

## ክፍል ሁለት

ዐቢይ ጉዳይ

በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን

## ክህነት እንዴት ይሾማል

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ "ኢኀደጋ ለምድር እንበለ ካህናት ወዲያቆናት፣ እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም፤ ቸሩ አምላክ እግዚአብሔር ለዘለዓለም እስከ ለዓለም ምድርን ያለ ካህናትና ዲያቆናት አልተዋትም" (ዚቅ ዘኀዳር ጽዮን) በማለት እንደገለጸው ክህነት ከጥንት ከአዳም ጀምሮ እንደነበረ በክፍል አንድ ተመልክተናል። በዚህ ክፍል ደግሞ ክህነት እንዴት ይሾማል የሚለውን እንመለከታለን።

የክህነት አሿሿም ሥርዓት በየዘመናቱ ይለያያል። ሿሚው ራሱ እግዚአብሔር ሁኖ የሚሾምበት ሥርዓት ግን እንደዘመናቱ ነባራዊ ሁኔታ የተለያየ እንደነበር መገንዘብ ይገባል። ለምሳሌ አዳምን በቀጥታ እግዚአብሔር ሾመው፤ መልከ ጼዴቅንም እንዲሁ በቀጥታ እግዚአብሔር ሾመው። አሮንና ከእርሱ በኋላ የነበረውን የክህነት አሿሿም ስንመለከት ደግሞ በሙሴ አማካኝነት ተሾሙ። ከዚያ በኋላ በዘር ማለትም ከሌዊ ወገን የሆነውን በዘመኑ የሚኖረው ሊቀ ካህን ሲሾም ኖሯል፤ ሐዋርያትን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሾማቸው፤ ከእነርሱ በኋላ ደግሞ ተከታዮቻቸውን እነርሱ እንዲሾሙ ታዝዘዋልና ሐዋርያት ሲሾሙ ኖረዋል፤ የእነርሱ ተከታዮችም እንዲሁ እየሾሙ ኖረዋል። የሐዲስ ኪዳኑ አማናዊ ክህነት ከሐዋርያት ጀምሮ ሐዋርያዊ ቅብብሎሹ ሳይቋረጥ እየተላለፈ ዛሬ ላይ ደርሷል።

ይህ ሐዋርያዊ ቅብብሎሹን ሳያቋርጥ ዛሬ ላይ የደረሰው የክህነት አሿሿም በአንብሮተ እድ ይከናወናል። በሐዋርያት ዘመን እንዴት እንደቀጠለ የሐዋርያት ሥራን የጻፈው ቅዱስ ሉቃስ "ወንድሞቻችን ሆይ ከእናንተ ወገን በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸውን ሰባት ሰዎችን ምረጡ፤ ለዚህ ሥራም እንሾማቸዋለን" (ሐዋ.፮፥፫) በማለት እንደነገረን ሐዋርያት እነርሱን በክህነት አገልግሎት እንዲያግዟቸው በሕዝብ ዘንድ የተመሰከረላቸውን፣ በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉትን ካስመረጡ በኋላ እንደሾሟቸው ያስረዳናል። የአሿሿም ሥርዓቱንም "በሐዋርያትም ፊት አቆሟቸው፤ ጸልየውም እጃቸውን በራሳቸው ላይ ጫኑ" (ሐዋ.፮፥፯) በማለት በምን ሥርዓት እንደተሾሙ ያስረዳናል። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ የወለደውን ጢሞቴዎስን "ስለዚህም ምክንያት እጄን በአንተ ላይ በመጫኔ ያገኘኸው የእግዚአብሔር ጸጋ ይታደስልህ ዘንድ አስብሃለሁ፤ የእግዚአብሔር የኃይልና የንጽሕና፣ የፍቅርና የጥበብ መንፈስን እንጂ የፍርሀት መንፈስን አልሰጠንምና" (፪ጢሞ.፩፥፮-፯) በማለት በምን ዓይነት ሥርዓት እንደሾመው ያስረዳናል። ይህ አማናዊው የሐዲስ ኪዳን ክህነት በክርስቶስ ተጀምሮ ወደሐዋርያት ተላልፎ ሐዋርያዊ ቅብብሎሹን ሳያቋርጥ እስከዚህ ዘመን ደርሷል በዚህ መንገድ እስከ ዓለም ፍጻሜም ይቀጥላል። የሐዲስ ኪዳን ክህነት በክርስቶስ መሥራችነት ከሐዋርያት የቀጠለና ሐዋርያዊ ለመሆኑ ተጨማሪ ማስረጃ እንመልከት።

ሐዋርያት ከራሱ ከሊቀ ካህናት ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበሉትን ክህነት እነርሱም በሰጣቸው በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ለተከታዮቻቸው አስተላልፈዋል። ይህ የሐዋርያት ክህነት ከእነርሱ ወደ ተከታዮቻቸው እንደተላለፈ በመጽሐፈ ዲዲስቅልያ እንዲህ ተገልጾ እናገኘዋለን። "በእኛም ዘንድ የተሾሙ ስማቸው ይህ ነው። መጀመሪያ በኢየሩሳሌም የተሾመ የጌታችን ወንድም ያዕቆብ ነው። ከእርሱም ቀጥሎ የቀለዮጳ ልጅ ስምዖን ነው።" በማለት የሁሉንም ስም ይዘረዝርና በመጨረሻም "በኢየሩሳሌም አምነን የሾምናቸው በየሀገራቸው ይሰብኩ ያስተምሩ ዘንድ የላክናቸው እሊህ ናቸው። የእነዚህን ድካማቸውን አስቡ፤ ምክራቸውንም ተቀበሉ፤ ቃላቸውንም ጠብቁ፤ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን፤ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለሙ" (መጽሐፈ ዲዲስቅልያ አንቀጽ ፴፫) ተብሎ ተጽፎ እናገኘዋለን።

ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ መድሎተ ጽድቅ በተባለው መጽሐፉ በቅጽ ሁለት ሐዋርያዊ ክህነትን በተመለከተ በስፋት አስረድቷል። ከመጽሐፉ መመልከቱ የተሻለ ግልጽ እንደሚያደርገው የታመነ ቢሆንም ለማሳያ ያህል እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

ሁሉም ምሥጢራት የሚፈጸሙት በካህናት ነው። ቤተ ክርስቲያን አስተዳደሯም ሳይቀር ሐዋርያዊ እንጂ በሙያቸው ወይም በሌላ መለኪያ ተወዳድረው ሥራ እንደሚቀጠሩባቸው እንደ ሌሎች ወይም ተቋማት አይደለም። ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደሯም ሐዋርያዊት ናት። ሁል ጊዜም የምትመራው የሐዋርያት ተከታዮች (ወራሾች) በሆኑ ጳጳሳት ነውና። ስለሆነም ክህነት ለቤተ ክርስቲያን ህልውና ቍልፍ (ጉዳይ) ነው። እንዲህ ከሆነ ይህ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልበት ክህነት ከቤተ ክርስቲያኗ መሥራችና ባለቤት ከጌታ የተገኘ ሊሆን የግድ ነው። ከጌታ የተገኘ ለመሆኑ ማረጋገጫው እና መለኪያው ምንድን ነው? ከተባለ ይህን የክህነት ጸጋ ከሊቀ ካህናት ከኢየሱስ ክርስቶስ ከተቀበሉ ከሐዋርያት እና እነርሱ ከሾሟቸው አባቶች ባልተቋረጠ ቅብብሎሽ የተገኘ ወይም የመጣ መሆኑ ነው።

**ሐዋርያዊ የሆነው ክህነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ከሐዋርያትና ከክርስቶስ ጋር በቀጥታ የሚያገናኛት መስመር ነው። ይህ የቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት እና ከክርስቶስ ጋር ያላት ቀጥተኛ ግንኙነትም አሳባዊ አንድነት ወይም የማይታይ ዓይነት አንድነት አይደለም።**

ይህ ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ የሆነ ቦታ ላይ ከተቋረጠ 'ክህነቱ' የሊቀ ካህናት የኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ቀረ ማለት ነው። እንዲህ ከተቋረጠ ደግሞ ማንም የክርስቶስ ክህነት ሊል አይችልም። አይሁድ ፋሲካቸው ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ስለነበረ ከእርሱ በተሰጡበት መንፈስና መንገድ ሲያከብሩ ሳለ "የእግዚአብሔር ፋሲካ" ተብሎ ይጠራ ነበር። (ዘፀ.፲፪፥፲፩፤ ዘሌ.፳፫፥፭፤ ዘኍ.፳፰፥፲፮) ከዚያ መንፈስና መንገድ ወጥተው በራሳቸው ስሜትና መንገድ ፋሲካን በማድረጋቸው "የአይሁድ ፋሲካ" ተባለባቸው። (ዮሐ.፪፥፲፫) እንደዚሁም ሁሉ ባልተቋረጠ ሐዋርያዊ ቅብብሎሽ ከመጣው ክህነት ውጭ "ክህነት አለኝ" የሚል ቢኖር ይህ ክህነት "የእገሌ ክህነት" ነው የሚባለው።

ሐዋርያዊ የሆነው ክህነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ከሐዋርያትና ከክርስቶስ ጋር በቀጥታ የሚያገናኛት መስመር ነው። ይህ የቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት እና ከክርስቶስ ጋር ያላት ቀጥተኛ ግንኙነትም አሳባዊ አንድነት ወይም የማይታይ ዓይነት አንድነት አይደለም። እንዲሁ በመጻሕፍት እና በታሪካዊ ኩነቶች ያለ ዕውቀት ብቻም አይደለም። በምሥጢረ ክህነት አማካኝነት ቀጥተኛ የሆነ ሕያው ግንኙነት ነው እንጂ። በዚህ ምሥጢር አማካኝነት ዛሬ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ሐረጓ ሲሰላና ሲመዘዝ ከሐዋርያት እና ከራሱ ከክርስቶስ ጋር ቀጥተኛ በሆነ ሕያው መስመር ያገናኛታል። ቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊት ከሚያሰኛት አንዱ ይህ ነው" (ያረጋል.፳፻፲፪ ገጽ ፬፻፸፱)።

ከላይ በሰፊው የቀረበው የዲያቆን ያረጋል ሐሳብ የሐዲስ ኪዳን ክህነት መሠረቱ ክርስቶስ ሆኖ በሐዋርያት ተቀባይነት ሐዋርያዊ ቅብብሎሹን ያላቋረጠ ይህን ሐዋርየዊ ቅብብሎሽ ካቋረጠ ደግሞ የግለሰቦች ክህት እንጂ የክርስቶስ ክህነት ሊባል እንደማይችል ያስረዳናል። ክህነት ይህ ዓይነት ቅብብሎሽ ስላለው ሀገራችን ኢትዮጵያ ከ፲፯፻ ዓመታት በላይ በቅርብ ሆኖ ጳጳሳትን፣ ካህናትን፣ ዲያቆናትን፣ የሚሾም፣ ቢያስፈልጋትም ሐዋርያዊ ቅብብሎሹን ላለማቋረጥ በእስክንድርያ ሥር ቆይታለች። በሁለቱ ሀገር መካከል ፖለቲካዊ ግጭት ሲፈጠር፣ የአሕዛብ ነገሥታት ሲነግሡና ጳጳስ ወደኢትዮጵያ እንዳይላክ ሲከለክሉ እስከ ሦስታና አራት መቶ ዓመታት ድረስ እየታገሠች ቆይታለች። ይህ ሁሉ ጥረት ሐዋርያዊ ቅብብሎሹ እንዳይቋረጥ ነው። ደግሞም

ክህነቱ አማናዊ የሚሆነው ሕጋዊ የሆነ ሿሚ ሲኖረው ነው። ክህነት እንደፖለቲካ ሹመት ተሰብስቦ በድምጽ ብልጫ፣ በብዙኃን ይሁንታ የሚሾሙት ሹመት አይደለም።

ፍትሐ መንፈሳዊ የክህነት አሿሿምን በተመለከተ በሰፊው ያትታል። ከሰፊ ሐተታው ውስጥ ግን ለዚህ ይሆናል ያልነውን እንደሚከተለው እንጠቅሳለን። "የሊቀ ጳጳሱ ሹመት የኤጲስ ቆጶሳትና የመጥሮጶሊሶች (ጳጳሳት) ጉባኤ ሳይሆን አይፈጸምም።" (አንቀጽ ፬ ቁጥር ፶፯) ይህ የሊቀ ጳጳሱስ ሹመት የሚመለከት ሲሆን የኤጲስ ቆጶሱንም ከኒቂያ ጉባኤ ቁጥር ፱ በመጥቀስ እንዲህ በማለት ገልጸውታል። "አንድ ሰው ኤጲስ ቆጶስነትን ሊሾም ቢፈልግ ሕዝቡም ቢስማሙ ያገሩ ጳጳስ ግን ባይፈቅድ ያለ እርሱ ፈቃድ ኤጲስ ቆጶስነት መሾም አይገባውም። ይህን ቢያፈርስ ሲኖዶስ ያወግዘዋል። ኤጲስ ቆጶስነቱም ይቀራል። ስለ እርሱ የሚበዙት ቢስማሙ ግን ጳጳሳቱም ቢስማሙበት በድምፅ ብልጫ ይሹሙት" (አንቀጽ ፭፥ቁ፺፩) "ያለ ኢጲስ ቆጶሱ ፈቃድ ቄስም ዲያቆንም አይሾም" (አንቀጽ ፭፥ቁ፻፲) በማለትም በተዋረድ ሊቀ ጳጳሱን ለመሾም የኤጲስ ቆጶሳትና የጳጳሳት ጉባኤ፣ ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም የሊቀ ጳጳሱ ፈቃድና የጳጳሳት ስምምነት ወይም ጉባኤ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ለመሾም ደግሞ የኤጲስ ቆጶሱ ፈቃድ እንደሚያስፈልግ ያስረዳል።

ሐዋርያት በመጽሐፈ ዲዲስቅልያ "ቀሳውስት፡- ዲያቆናትንና ዲያቆናዊትን፣ አናጉንስጢስንም፣ መዘምራንንም በር ዘጊዎችንም እንዳይሾሙ እናዝዛለን። እነሆ አስቀድመን ነግረናቸው እንደዚህ የሚያደርጉ ሰዎች ከክርስቲያን ወገኖች የተለዩ ይሆናሉና። (ዲዲስቅልያ አንቀጽ ፲፭፥፳-፲) በማለት ቀሳውስት እንኳንስ ከእነርሱ በላይ ያለ መዐርገ ክህነትን ከእነርሱ በታች ያሉ ዲያቆናትን እና አናጉንስጢሶችንም እንዳይሾሙ ተከልክለዋል። በቅዱስ ወንጌል ጌታችና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በንጉሥና በአገልጋይ መስሎ ባስተማረው ትምህርት ባለ አንድ፣ ባለሁለትና ባለ አምስት ብሎ በምሳሌ ያስተማረውን ትምህርት መምህራን ሲተረጉሙት ባላንድ ዲያቆን ግብሩ ተልእኮ ብቻ ነውና፣ ባለሁለት ቄስ ግብሩ ማጥመቅና ማቁረብ ነውና ባለአምስት ጳጳስ ግብሩ ማጥመቅ፣ ቀድሶ ማቁረብ፣ ካህናትን ዲያቆናትን መሾም… ነውና ብለው ተርጉመውት እናገኛለን። ስለዚህ ክህነትን ለመሾም የግድና የግድ ጳጳስ መኖር አለበት። የሚሾመው ጳጳስ ከሆነ ሦስትና ከዚያ በላይ ጳጳሳት፣ ቄስና ዲያቆን ከሆነ ግን አንድም ቢሆን ጳጳስ መኖር አለበት።

በዘመናችን እንዲሁ በዘፈቀደ ጳጳስ ሹመናል፤ ፓትርያሪክ ሹመናል እየተባለ የሚወራው ወሬና እንቅስቃሴ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ከሐዋርያት ቀኖና እጅግ የማይገናኝ እንዲሁም የሐዋርያትንና የሊቃውንትን ቀኖና የጣሰ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባዋል። በቀሳውስት ተሾሙ እንዳይባል የቀሳውትን ድርሻ ግልጽ በሆነ መልኩ ያስቀምጥልናል። በፍትሐ መንፈሳዊ "ለቄስ አንድ ሥልጣን ብቻ አለው። ይኸውም ያስተምር ዘንድ፣ ያጠምቅ ዘንድ፣ ይቀድስ ዘንድ፣ ይባርክ ዘንድ ነው።… አንዱን ስንኳ አይሹም፣ አይሻረውም" (አንቀጽ ፮ ቁጥር ፪፻፲፭) በማለት መሾም መሻር የቀሳውስት ድርሻ እንዳልሆነ ያስረዳናል። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች በማን ተሾሙ የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ መመለስ ይኖርባቸዋል።

በራሳችን ተሾምን ካሉ ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ራሳቸው መሾም አይችሉም በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከላይ እየገለጽነው እንደመጣነው ሐዋርያዊ ቅብብሎሹን አቋርጧልና የክርስቶስ ክህነት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም የሐዲስ ኪዳን ክህነት እንደፖለቲካዊ ሥልጣን በሕዝበ ውሳኔ የሚሾሙት እንዳልሆነ መሠረቱ ክርስቶስ ሆኖ በሐዋርያት በኩል ዛሬ ላይ የደረሰ አማናዊ ክህነት መሆኑን በሰፊው ገልጸናል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንዲሁ ተነሥተው ተሹሚያለሁ፣ ወይም ሾመናል የሚሉት እንዳልሆነ በሰፊው አይተናል። እንኳንስ እንዲህ ሊሉበት የራሱን ክብር ከመፈለግ አንጻር እኔ ሳልመጣ ለምን ሾማችሁ ብሎ ክህነቱን በያዘበት ጊዜ እንኳን ክህነቱን የያዘበትን አባት በምን መንገድ እንዳሸነፈው የሚያስታውሰን አንድ ታሪክ እንስታውስ።

## አባ አትናስዮስ

ይህ ቅዱስ ከታናሽነቱ ጀምሮ መነኰሰ ባሕታዊም ሆኖ የሚያገለግል ቅን ትሑት በበጎ ሥራ ሁሉ ፍጹም ሆነ።

ሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤልም ካረፈ በኋላ ኤጲስ ቆጶሳት ሁሉም ተሰበሰቡ ይህንንም አባት ሊቀ ጵጵስና ይሾሙት ዘንድ መረጡት። ፈጥኖም እንዲመጣና ከእነርሱ ጋር ይህን አባት እንዲሾም ወደ ሀገረ ሰልቅ ሊቀ ጳጳስ ወደ አባ

እልመፍርያን ላኩ። እርሱ ግን መምጣትን ዘገየ። እነርሱም ሃምሳ ቀኖች ያህል ጠብቀው አባ አትናስዮስን ሹመውት ወደየሀገረ ስብከታቸው ተመለሱ። ከዚህም በኋላ በላኩበት መሠረት ሊቀ ጳጳሳት አባ እልመፍርያን መጣ። ወደ ሶርያም ድንበር ሀገረ ዓምድ ደረሶ ከአንድ ጳጳስ ጋር ተገናኘ። ያም ጳጳስ እርሱ ከመምጣት በዘገየ ጊዜ አባ አትናስዮስን እንደሾሙት ነገረው በሰማም ጊዜ እጅግ ተቆጣ እንዲህም አለ በእኛና በእናንተ መካከል ያለውን ሕግ እንዲህ ትሽራላችሁን ይህንም ብሎ በቍርባንም ቢሆን ወይም በማዕጠንት የአባ አትናስዮስን ስም የሚጠራውን ሁሉ አውግዞ ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

አባ አትናስዮስም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ ረዳቱንም ጠርቶ እንዲህ አለው ልቤ ትባርክህ ትመርቅህ ዘንድ ታዘዘልኝ ሕዝቡ የፈለጉኝ እንደሆነ በዋሻ ሱባዔ ውስጥ ነው በላቸው እኔ ወደአንድ ቦታ ሔጄ አንድ ዓመት ያህል እቆያለሁና አንተም ሊሆን በሚገባ ሥራ ሁሉ እዘዛቸው በእኔም ፈንታ እሰር ፍታ እረዳቱም እሺ አለው።

**ክህነት ይህ ዓይነት ቅብብሎሽ ስላለው ሀገራችን ኢትዮጵያ ከ፲፮ ዓመታት በላይ በቅርብ ሆኖ ጳጳሳትን፣ ካህናትን፣ ዲያቆናትን፣ የሚሾም፣ ቢያስፈልጋትም ሐዋርያዊ ቅብብሎሹን ላለማቋረጥ በእስክንድርያ ሥር ቆይታለች።**

ከዚህም በኋላ አባ አትናስዮስ የድሀ ልብስ ለብሶ በሥውር ወጣ በእግሩም ሔደ ወደ ሀገረ ሰልቅ ደረሰ። የሊቀ ጳጳስ አባ እልመፍርያንን ደጅ አንኳኳ በረኛውም ምን ትሻለህ አለው። ከሊቀ ጳጳሱ ቡራኬ እሻለሁ ብሎ መለሰለት ነግሮለትም አስገባው። አባ እልመፍርያን አንተ ከወዴት ነህ አለው። ከሶርያ ሀገር ነኝ የዕለት ሲሳይና ልብስ አጥቼ መጣሁ በጥላህም ሥር ሁኜ ላገለግል እሻለሁ ብሎ መለሰ።

ሁለተኛም ቄስ ነህን ወይስ ዲያቆን አለው እርሱም አይደለሁም አለ። ሹሙንም ጠርቶ ከመነኮሳቱ ጋር እንዲአኖረው አዘዘው። አባ አትናስዮስም የሊቀ ጳጳሱን የቤት ውስጥ ሥራ የፈረሶችንና የበቅሎዎችን ፍግ  እስከሚጠርግ የሚሠራ ሆነ ይፈጫል ውኃ ይቀዳል እንጀራ ይጋግራል ወጥ ይሠራል ምንም ምን ሥራ አይቀረውም። እንዲሁም ለመነኰሳቱ ቤታቸውን ይጠርግላቸዋል ውኃንም ይቀዳላቸዋል እሳትንም ያነድላቸዋል እጅግም ስለወደዱት እንደ ሰማያዊ መልአክ አስመሰሉት።

ከዚህ በኋላ አትናስዮስን ዲቁና ይሾመው ዘንድ ሊቀ ጳጳሱን መነኰሳቱ ማለዱት፤ በእሑድም ቀን አባ እልመፍርያን ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ዲቁና ሊሾመው አባ አትናስዮስን ጠራው። እርሱም አባቴ ሆይ ተወኝ እኔ ድሀ ነኝና አለው ባልተወውም ጊዜ አባቴ ይቅርታ አድርግልኝ ይህስ ዲቁና አለኝ አለው። ሊቀ ጳጳሱም ከትዕግስሥቱና ከትሕትናው የተነሣ አደነቀ በዲቁናም እንዲአገለግል አዘዘው በዲቁና እያገለገለ ሰባት ወር ኖረ።

ሊቀ ጳጳሱ አዋቂነቱን አይቶ ቅስና ሊሾመው ወደደ። በእሑድ ቀንም  ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠርቶ መንፈስ ቅዱስ ቅስና ሊሾምህ መርጦሃል አለው። አባ አትናስዮስም ሰምቶ አለቀሰ እንዲተወውም ማለደው። ባልተወውም ጊዜ አባቴ ይቅር በለኝ እኔ ቄስ ነኝ አለ መነኰሳቱም ሁሉ አደነቁ በእርሱም ደስ አላቸው።

አባ እልመፍርያንም አስተዋይነቱን የአንደበቱን ጣዕም የተደራረበ አገልግሎቱንም ተመልክቶ ጳጳሷ ለሞተባት ለአንዲት ሀገር ጵጵስና ሊሾመው ወደደ። ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን ቀሳውስትንና ዲያቆናትንም በእሑድ ቀን ሰበሰባቸው አባ አትናስዮስንም አቅርበው እንዲህ አሉት ለእገሌ ሀገረ

ስብከት ጳጳስ ልትሆን ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ጠርቶሃል አሉት፡፡ እርሱም ሰምቶ አለቀሰ፡፡ እንዲተውትም አልቅሶ አማላቸው እንደማይተውትም በአወቀ ጊዜ እርሱ የአንጾክያ ሊቀ ጳጳሳት አትናስዮስ እንደሆነ ነገራቸው የአመጣጡንም ምሥጢር ገለጸላቸው፡፡

በዚያንም ጊዜ አባ እልመፍርያን ደነገጠ አክሊሉንም ከራሱ ላይ አውልቆ በምድር ላይ ወደቀ፡፡ ለረጅም ጊዜ እንደሞተ ሆነ በተነሣም ጊዜ እንዲህ ብሎ ጮኸ ወንድሞቼ የማደርገውን እስቲ ንገሩኝ ዛሬ እሳት ከሰማይ ወርዶ እንዳያቃጥለኝ ምድርም አፍዋን ከፍታ እንዳትውጠኝ እፈራለሁና ጌታየ የአንጾክያ ሊቀ ጳጳስ አትናስዮስ ውኃ እየቀዳ የፈረሶችና የበቅሎዎች ጉድፍ እየጠረገ በቤቴ ውስጥ እንደባርያ ሊያገለግል አግባብ ነውን ወዮልኝ ወዮልኝ፡፡

ጳጳሳቱ የተሰበሰቡት ሁሉ በሰሙ ጊዜ ከእግሩ በታች ወድቀው ሰገዱለት እጆቹንና እግሮቹንም ሳሙ ሊቀ ጳጳሱም ያማሩ የክህነት ልብሶችን ያለብሱት ዘንድ መስቀሎችንና አርዌ ብርቱን ያመጡ ዘንድ በመንበር ላይ ያስቀምጡት ዘንድ አዘዘ፡፡

ከዚህም በኂላ ጳጳሳቱ ከመንበሩ ጋር ተሸከሙት ሦስት ጊዜ አክዮስ አክዮስ አክዮስ እያሉ ይህም ይገባዋል ማለት ነው ቤተ ክርስቲያኑን አዙረው ወደ መቅደስ አስገቡት፡፡ ከዚህም በኂላ መቀደሻ ልብስ ለብሶ መሥዋዕቱን አክብሮ ቀድሶ አቆረባቸው እነርሱንም ሀገራቸውንም ባረከ ለዚያችም አገር ምንኛ መጠን የሌለው ደስታ ሆነ፡፡

በማግሥቱ አባ እልመፍርያን ተነሥቶ በቅሎ አስመጣ ለጉዞ የሚያሻውን ሁሉ አዘጋጀ አባ አትናስዮስንም በበቅሎ አስቀምጦ እርሱ በእግሩ ተከተለው ጳጳሳቱና ኤጲስ ቆጶሳቱ ሁሉም ከአባ እልመፍርያን ጋር አጅበው ወደ አንጾክያ ሀገር ወሰዱት፡፡ አባ አትናስዮስም አባ እልመፍርያንን አንተም በበቅሎ ላይ ተቀመጥና በአንድነት እንሒድ አለው፡፡ አባ እልመፍርያንም ጌታዬ ለእኔ አይገባኝም አንተ በእግርህ ወደ ሀገሬ እንደመጣህ እንዲሁ እኔም በእግሬ ወደ ሀገርህ አደርስሃለሁ አለው፡፡

የአንጾክያ ሀገር ጳጳሳትም የሊቀ ጳጳሳት አትናስዮስን መምጣት በሰሙ ጊዜ ከሕዝብ ሁሉ ጋር ሊቀበሉት ወጡ በታላቅም ክብር ተቀብለው ወደሹመቱ መንበር አስገቡት፡፡ ለአባ እልመፍርያንም ሁለተኛ ወንበር አድርገው በክብር አስቀመጡት በዚያችም ቀን ፈጽሞ ደስ አላቸው ተሰናብተውትም ወደ ሀገራቸው በፍቅር በአንድነት ተመለሱ፡፡ ይህም አባት አትናስዮስ በጎ አኗኗርን ኖረ መንጋውንም በትክክል በእውነት ጠበቀ በጎ ጉዞውንም ፈጽሞ በሰላም አረፈ፡፡ (ምንጭ ስንክሳር ጥቅምት ዘጠኝ ቀን)

ከዚህ ታሪክ የምንማረው ከሊቀ ጳጳሳት አባ አትናስዮስ ብቻ ሳይሆን ከሊቀ ጳጳሳት አባ እልመፍርያንም ነው፡፡ ምክንያቱም የአባ አትናስዮስን ትሕትና እና ትዕግሥት ባየ ጊዜ ራሱንም ዝቅ አድርጎ ላጠፋው ጥፋት ይቅርታ ጠይቋል፡፡ ለእኛም ከቅዱሳን አባቶች ከአባ አትናስዮስና እና ከአባ እልመፍርያን ረድኤትና በረከት የቅዱሳን አምላክ ያሳድርብን አሜን፡፡

ከላይ በቀረበው ታሪክ ግሩምና ድንቅ የሆነ የትሕትና ሥራ እንደምንማር ሁሉ በአንጻሩ ደግሞ ሥልጣነ ክህነቱ ሳይኖረው በድፍረት የክህነት አገልግሎት እያከናወነ የነበረውን ሰው ምን ዓይነት ቅጣት እንደደረሰበት እንመልከት፡፡

ብህንሳ በምትባል ሀገር ይኖር የነበረ አንድ ሰው

ብህንሳ በምትባል ሀገር ከአንድ ገዳም  የነበረ አበ ምኔት በጽኑዕ ታሞ ሳለ አባ ለትጹን ወደ እርሱ ሲሄድ መነኮሳቱ በዙሪያው  ሲያለቅሱ አገኛቸው፡፡ መነኮሳቱን አስወጥቶ ብቻውን ሲጠይቀው እርሱ የሠራውን ኃጢያት ማንም እንዳልሠራው ነገረው፡፡ ከሠራቸው ኃጢያቶች የተወሰኑት ክህነት ሳይሾም እንደተሸመ ሆኖ የቅስና አገልግሎቱን ማገልገል፣ የጠላቸውን ሰዎች ደግሞ በቊርባኑ ላይ መርዝ እያደረገ መግደል፣ከእናቱ ጋር ግንኙነት መፈጸም፣በጸነሰች ጊዜ መርዝ አጠጥቶ ጽንሡን መግደል ወዘተ. የሚሉት ነበሩ፡፡ አባ ለትጹን የዚህን አበምኔት ኃጢያት ከሰማ በኂላ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው አብዝቶ መጸለይ ጀመረ፤ እግዚአብሔር ግን ኃጢያቱ እጅግ የከፋ ነውና ይቅር እንደማይለው በመልአኩም እርሱም ተገልጾ ነገረው፡፡ አባ ለትጹን ግን እርሱን ይቅር የማትለው ከሆነ እኔንም አብረህ ወደሲኦል አውርደኝ ብሎ ለመነ፡፡ ስለ አባ ለትጹን ቅድስና

እና ትጋት የሰውዬውን ነፍስ እንዳልነበረች አደረጋት (ስንክሳር፣ሰኔ ፲፯)

መቼም ስርየተ ኃጢያት የማይደረግለት ኃጢያት ከተሠራ እጅግ ከባድ ነው። ግን ሰውየው የፈጸማቸው ኃጢያቶች ለመስማትም ለመናገርም የሚዘገንኑ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ በዋናነት ለክህነት የነበረው ድፍረት፣ ሳይካን አገልግሎት መፈጸም፣ ሰው አድንበታለሁ፣ እኔም እድንበታለሁ ብሎ በትሕትና በንጽሕና ማገልገል ሲገባው በድፍረት በሥጋ ወደሙ ላይ መርዝ እያደረገ ሰው መግደል። ክህነት አለኝ ብሎ በክህነት እያገለገለ ከእናቱ ጋር ዝሙት መፈጸም፣ ካህን የታመሙትን የሚፈውስ፣ ለሞቱት የሚጸልይ፣ የሕዝብ አገልጋይ ነው እርሱ ግን ነፍሰ ገዳይ በእነዚህ ሁሉ አገልግሎቶች የፈጸማቸው ኃጢያቶች የተደራረቡና በርከተ ያሉ ናቸው። ይህም ሁሉ ክህነትን እንዴት በድፍረት እንደ ቀለደበት የሚያመለክት ነው። የዚህ የድፍረት ውጤቱ ደግሞ እንዲህ ዓይነት መዓትን አስከተለበት።

ዛሬም ሰዎች ክህነትን እጅግ ከመደፋፈራቸው የተነሣ ሳይሾሙ ተሾመናል የሚሉ፣ ሹመታቸው በቅዱስ ሲኖዶስ ተይዞባቸውም በድፍረት የክህነት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ሰዎችን እያስተዋልን የምንገኝበት ዘመን ነው። መቼም የኃጢያት መጀመሪያ ባይሆንም በመደፋፈራቸው ቅጣት እንደደረሰባቸው፣ ባለመደፋፈራቸውና በትሕትና መንገድ በመጓዛቸው ደግሞ የትሕትና በረከትን ያገኙ ሰዎችን ታሪክና ሕይወት እየተማርን ከስሕተቱም ሆነ ከመልካም ሥራቸው የማንማር ከሆነ በአመፃችን የበለጠ ልንቀጣበት እንደምንችል መረዳት ይኖርብናል።

በክህነት አገልግሎት እያገለገሉ ያሉት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አለመሾማቸውን እና ክህነታቸው ተይዞባቸው በድፍረት እያገለገሉ እንደሆነ እያወቀ በእነርሱ የሚገለገለው ምእመንም ከተጠያቂነት እንደማይድን፣ የጥፋተኞች የግብር አበር መሆኑንና ቅጣቱ እንደሚያገኘው መረዳት ይኖርበታል። ክቡርና ታላቅ የሆነውን የእግዚአብሔር ጸጋ በምንችለው መጠን ተረድተነውና አክብረነው በአግባቡ ተገልግለንበት የመንግሥቱ መውረሻ እንዲያደርግልን እግዚአብሔር ይርዳን አሜን። ይቀጥላል...

**በክህነት አገልግሎት እያገለገሉ ያሉት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አለመሾማቸውን እና ክህነታቸው ተይዞባቸው በድፍረት እያገለገሉ እንደሆነ እያወቀ በእነርሱ የሚገለገለው ምእመንም ከተጠያቂነት እንደማይድን፣ የጥፋተኞች የግብር አበር መሆኑንና ቅጣቱ እንደሚያገኘው መረዳት ይኖርበታል።**

# ቶማስ ዘመርዓስ

## እናስተዋውቃችሁ

*በቀሲስ ዘክርስቶስ ጸጋዬ*



በቶማስ  ስም የሚጠሩ በኦርቶዶክሳዊት  ቤተ ክርስቲያን የሚታወቁ በርካታ ቅዱሳን ቢኖሩም የዚህ  ዓምድ ዋና ትኩረቱ የክርስቶስ ምስክሩና ሐዋርያው የሆነ የመርዓስ ኤጲስ ቆጶስ ተጋዳይ ቶማስ ላይ አድርጎ ዘመናችንን ይፈትሻል።

የቅዱስ ቶማስ ዘመርዓስ ትሩፋትና ገድሉን ሰው ተናግሮ ሊፈጽመው አይቻልም እርሱ አስቀድሞ ከልጅነቱ ቅዱሳት መጻሕፍትን የተማረ፣ ገና በወጣትነቱ መንኖ  ገዳም የኖረ፣ በጾም፣ በጸሎት፣ በሰጊድ፣ ቀን እና ሌሊትም በመትጋት ለድኆችና ለምስኪኖችም በመራራት ተጠምዶ የኖረ ነበር።

ቅዱስ ቶማስ "መርዓስ" በምትባል አገር የወጣ የንጋት ኮከብ፣ ጻድቅ፣ ገዳማዊ፣ ጳጳስ፣ ሐዋርያ፣ ሰማዕትና ሊቅ ነው። የእርሱ ሕይወት ኦርቶዶክሳዊ የክርስትና ሕይወትና የጽጽስና የሹመት ሕይወት ምን እንደ ሆነ በትክክል የሚያሳይ ነው። መርዓስ በምትባል ሀገር ጳጳስ ሆኖ ተሹሞ በእረኝነት ያገለገል ዘንድ የክብር ባለቤት ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መረጠው መንጋውንም እንደ ሐዋርያት ጠበቀ።

በሹመት ዘመኑ በሰላሙም በመከራውም  ዘመን ‹‹ መኑ ያኀድገነ ፍቅሮ ለክርስቶስ ፤ ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል?›› (ሮሜ ፰፥፴፭-፴፯) እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ ለክርስቶስ ያለውን ፍቅር መከራ፣ ጭንቀት፣ ስደት፣ ራብ፣ ራቁትነት፣ ፍርሃት፣ ሰይፍ ሳይለየው ለአርባ ዓመታት ስለ ክርስቶስ ቀኑን ሁሉ እንደሚታረድ በግ ሆኖ እግዚአብሔርን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አገለገለ።

ቅዱስ ቶማስ ዘመርዓስ በሐዋርያዊ አገልግሎቱ ብዙ አሕዛብን ወደ ክርስትና የመለሰ እና በዘመነ ሰማዕታት ብዙ መከራን የተቀበለ አባት ነው። ጨካኞቹ ቅዱሱን ለ፳፪ ዓመታት አካሉን እየቆራረጡ ለጣዖታቸው ያጥኑ ስለ ነበር ፪ እግሮቹ፣ ፪ እጆቹ፣ ፪ ጆሮዎቹ፣ ፪ አፍንጫዎቹ እና ፪ ዐይኖቹ አልነበሩም። ነገር ግን እንዲህም ሆኖ አልሞተም እግዚአብሔርንም ማገልገለ አልተወም ነበር። በመጨረሻም በዘመነ መናፍቃን አርዮስን ካወገዙት ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት አንዱ ለመሆን የበቃ ነበር።

የስንክሳር አርኬ ደራሲው አርከ ሥሉስም ስለ ቶማስ ዘመርዓስ ለሌሎቹ ቅዱሳን እንደጻፈላቸው ሁሉ ‹‹ሰላም ለቶማስ ዘአባላቲሁ ግሙድ፣ እስከ አስተርእየ ኀብሩ አምሳለ ውዑይ ጕንድ፣ ለዝ መዋዒ በነጽሮ ገድሉ ፍድፉድ፣ ወሰላም ለእለ ምስሌሁ ሙቁሐነ እድ፣ አእላፈ ክርስቶስ ተስዓቱ እልፍ በፍቅድ፤ ሰውነቱ እንደደረቀ ግንድ እስኪመስል ደድረስ አካላቱ ለተቆረጡ ለቶማስ ሰላምታ ይገባል። የዚህን የአሸናፊ ቶማስን የበዛ ገድሉን በማየት በፈቃድ ከእርሱ ጋር ለታሰሩትና የክርስቶስ ወገኖች ለሆኑ ለዘጠኝ እልፍም ሰላምታ ይገባል።›› በማለት አርኬ ደርሶለታል።

ምንም እንኳን በአቡነ ተክለ ሃይማኖትና በቶማስ ዘመርዓስ የዕረፍት ቀን  በመካከላቸው የ ፩ሺህ ዓመት ልዩነት ቢኖርም የአቡነ ተክለይማኖት መልክእ ደራሲው ዮሐንስ ከማ ሁለቱ ቅዱሳንን በማነጻጸር ‹‹ሰላም ለጸአተ ነፍስከ በስብሐተ አእላፍ እንግልጋ፣ ለዓለመ ዛቲ እም ግብርናቲሃ

ወጹጋ፣ ተክለሃይማኖት ቶማስ ለመርአስ ዐቃቤ ሕጋ ለእመ ገብሩ ተዝካረከ እለ ሀለዉ በሥጋ ፣ ሀቦሙ እግዚእየ ሞገሰ ወጸጋ፤ የመርዓስ የሕጉ ጠባቂ ቶማስ ተክለ ሃይማኖት ሆይ ከዚች ዓለም ሥራና ድካም በአእላፍ መላእክት ምስጋ ለነፍስህ መውጣት ሰላምታ ይገባል፡፡ በሥጋ ሳሉ ተዝካርህን ያደረጉትን ጌታየ ሆይ ሞገስንና ጸጋን ስጣቸው፡፡›› በማለት ጽፏል፡፡

ከሃዲው ዲዮቅልጥያኖስ በነገሠ ጊዜ ክርስቲያኖቹን ሲያሰቃዩ በነበረበት ወቅት ከንጉሱ መኳንንት አንዱ ወደ መርዓስ ሄዶ ቶማስ ዘመርዓስን በጭፍሮቹ አስያዙት፡፡ እንደያዙት ደብድበው በምድር ላይ እየጎተቱት ደሙ እየፈሰሰ ወሰዱት፡፡

መኰንኑ ቅዱስ ቶማስን ‹‹ለአማልክት ስገድ›› አለው፡፡ ቶማስ ዘመርዓስም ‹‹እኔ ከሕያው እግዚአብሔር ልጅ ከጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ለረከሱ ጣዖታት አልሰግድም ለረከሱ ጣዖታት የሚሰግድ ሁሉ የተረገመ ነውና ከእግዚአብሔር በቀር የሚሰግዱለት አምላክ የለም ›› አለው፡፡

መኰንኑም እጅግ የብዙ ጽኑ ስቃዮችን አሰቃየው፡፡ የነዳጅ ድፍድፍ አፍልተው በሰውነቱ ላይ እንዲሁም በአፍና በአፍንጫው ውስጥ ጨመሩበት እስከ ብዙ ዘመናት ኖረ፡፡ እነዚህ ከሀድያን ልባቸው እንደ ደንጊያ የጸና ስለነበረ ቶሎ ብለው እንዲሞቱ ሳይሆን በሥቃይ ሆነው እንዲቆዩ በማድረግና ሌሎች ብዙዎች ሰዎችን ያስፈሩአቸው ዘንድ የክብር ባለቤት ክርስቶስን ይክዱ ዘንድ የሥቃዩን ዘመን አስረዘሙት፡፡

ቶማስ ዘመርዓስ ግን በጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል የጸና ነውና ማሰቃየቱን ከሃዲያን በደከማቸው ጊዜ ስለስሕተታቸው ይዘልፋቸው ስለ ነበር ወደ ጨለማ ቦታ ጣሉት በዚያም ለ፳፪ ዓመታት በጨለማ ውስጥ አስረው አሠቃዩት፡፡ ከሀድያኑም በየዓመቱ ወደ እስር ቤቱ እየገቡ አንድ አካሉን ይቆርጣሉ፡፡

‹‹መተሩ አንፎ፣ ወከናፍሪሁ፣ ወእዘኒሁ፣ ወእደዊሁ፣ ወእገሪሁ፣ ወመሰሎሙ ለመርዓቱ ዘአዕረፈ ወነበሩ እንዘ ይገብሩ ተዝካሮ ለለዓመት፤ አፍንጫውን ከንፈሮቹን ጆሮዎቹን እጆቹንና እግሮቹን ቆረጡ መንጋዎቹም ያረፈ መስሏቸው በየዓመቱ መታሰቢያውን ሲያድርጉ ኖሩ፡፡››

ከሃዲያኑ እጅና እግሩን በየተራ የቆራረጡትን የሰውነት አካላቱን አፍንጫውን፣ ከንፈሮቹን፣ ጆሮዎቹን ሁሉ በየተራ እየቆረጡ ለ ፳፪ ዓመታት ጣዖታቸውን ሲያጥኑበት ኖረዋል፡፡

አንዲት ደግ ክርስቲያናዊት ሴት ቶማስ ዘመርዓስ የተጣለበትን ጉድጓድ አይታ ስለነበረ በድብቅ በሌሊት ተሰውራ እየሄደች ትመግበው ነበር፡፡ ደገኛውና ጻድቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እስከ ነገሠና የቀናች የክርስቶስን ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖትን ክብር እስከ ገለጠበት ድረስ ቶማስ ዘመርዓስ ሲሰቃይ ቆየ፡፡

ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመታመኑ የታሠሩ እሥረኞችን ሁሉ በሀገሮች ሁሉ በወህኒ ቤት ያሉትን ይፈቷቸው ዘንድ አዋጅ አውጥቶ ሲያዝ ክርስቲያናዊቷ ሴት ሄዳ ስለ ቅዱስ ቶማስ ስለ እርሱ የሆነበትን ሃያ ሁለት ዓመት ተጥሎ እንደኖረ ለካህናቱ ነገረቻቸው በውስጡ ወደ ሚኖርበትም ቦታ መራቻቸው፡፡

**መኰንኑ ቅዱስ ቶማስን ‹‹ለአማልክት ስገድ›› አለው፡፡ ቶማስ ዘመርዓስም ‹‹እኔ ከሕያው እግዚአብሔር ልጅ ከጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ለረከሱ ጣዖታት አልሰግድም ለረከሱ ጣዖታት የሚሰግድ ሁሉ የተረገመ ነውና ከእግዚአብሔር በቀር የሚሰግዱለት አምላክ የለም›› አለው፡፡**

ካህናቱም አንሥተው ተሸከሙት እየዘመሩና እያመሰገኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን አደረሱት፤ በቤተ መቅደሱም ፊት ለፊት በወንበሩ ላይ አስቀመጡት፤ ምእመናንም ሁሉ ወደእርሱ እየመጡ ከእርሱ ይባረኩና የተቆረጠ አካላቱን ይሳለሙ ነበር፡፡

ቶማስ ዘመርዓስ ወደ ሠለስቱ ምዕት ጉባኤ ሲሄድ ዞሮ እንዳያስተምር እግሩን፣ ጽፎ መልእክታት እንዳይልክ እጁን፣ በሰማእትነት በሃያ ሁለት ዓመታቱ ሰማእትነት አስጥቶአቸው ስለነበር፤ ደቀ መዛሙርቱ በቅርጫት ውስጥ አድርገው በአህያ ጭነው ወደ ጉባኤ ኒቂያ ይዘውት ሄደዋል፡፡

በመንገድም ሳሉ ዐላውያን አግኝተዋቸው ጥቁርና ነጭ አህዮቻቸውን ሌሊት ራስ ራሳቸውን ቆርጠው ጣሉባቸው፡፡ በማግስቱም ቶማስ ዘመርዓስም ራሳቸውን የተቆረጡትን አህዮች አምጡልኝ ብሎ የጥቁሩን አህያ ራስ ከነጩ፣ የነጩን አህያ ራስ ለጥቁሩ ገጥሞ ቢባርካቸው ሁሉም አህዮች ከሞት ተነስተዋል፡፡ የአህዮቻቸውም መልክ እጅግ ያማሩ ሆኑ፡፡

ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ የከበሩ የሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ኤጲስቆጶሳቱን በኒቂያ ሀገር እንዲሰበሰቡ ሲያደርግ ይህ የከበረ ቶማስ ዘመርዓስ ከሊቃውንቱ አንዱ ነበር፡፡ ከጉባኤው ሲደርሱ ንጉሡ ቈስጠንጢኖስ ወደ ጉባኤው ገብቶ ለቅዱሳን ሊቃውንቱ ሰላምታ ሰጣቸውና ከሊቃውንቱ ቡራኬ ተቀበለ፡፡ የዚህን ቅዱስ የቶማስ ዘመርዓስን ተጋድሎውን በነገሩት ጊዜ ወደ እርሱ ቀርቦ ሰገደለት፤ አካላቱም ከተቈራረጡበት ላይ ተሳለመው፡፡ ከዚያም አዝኖና አጅግም ተደንቆ አድንቆ አካላቱን ዳሠሠው ፊቱንና ዓይኖቹን አሻሸው ጽድቁንም ዐውቆ ‹‹ አባቴ በረከትህ ትድረሰኝ ›› በማለት ተባርኳል፡፡

ትምህርተ ሃይማኖትን፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ካጸና በኋላ ወደ ሀገረ መንበረ ሢመቱ ተመልሶ ካህናቱንና መንጋዎቹን ሁሉ ሰብስቦ ጸሎተ ሃይማኖትን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አነበበላቸው ይኅን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንም አጽንተው እንዲጠብቁት አዘዛቸው፡፡ ጥቂት ዘመናትም ከኖረ በኋላ ቅዱስ ቶማስ ጵጵስና በተሾመ በ፶ ዓመቱ ነሐሴ ፳፬ አርፏል፡፡ የጻድቃንን፣ የሰማዕታትን፣ የሐዋርያትንና የሊቃውንትን አክሊልም ተቀብሏል፡፡

*(ምንጭ ስንክሳር ዘወርኃ ነሐሴ)*

*አምላከ ቅዱስ ቶማስ ዘመርአስ በረድኤቱ አይለየን!!!*

**በመንገድም ሳሉ ዐላውያን አግኝተዋቸው ጥቁርና ነጭ አህዮቻቸውን ሌሊት ራስ ራሳቸውን ቆርጠው ጣሉባቸው፡፡ በማግስቱም ቶማስ ዘመርዓስም ራሳቸውን የተቆረጡትን አህዮች አምጡልኝ ብሎ የጥቁሩን አህያ ራስ ከነጩ፣ የነጩን አህያ ራስ ለጥቁሩ ገጥሞ ቢባርካቸው ሁሉም አህዮች ከሞት ተነስተዋል፡፡ የአህዮቻቸውም መልክ እጅግ ያማሩ ሆኑ፡፡**

# የጥያቄዎቻችሁ መልስ



**በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን**

*በጥያቄዎቻችሁ መልስ ዓምዳችን ወርኀ ጳጕሜንና የዘመን መለወጫ (ዕንቁዕጣጣሽን) በተመለከተ የሚነሡ ጥያቄዎችን መሠረት አድርገን ምላሽ ይሰጡን ዘንድ በማኅበረ ቅዱሳን መደበኛ አገልጋይ የሆኑትን አባ ዐሥራተ ማርያም ደስታን ጋብዘናቸዋል፡፡ ቆይታችንን እንዲህ አዘጋጅተነዋል፤ መልካም ቆይታ፡፡*

***ሐመር፡-*** አባታችን የምናነሣቸው ጥያቄዎች ከጳጕሜንና ከዘመን መለወጫ ጋር የተያያዙ ይሆናሉ፡፡ ለመሆኑ ጳጕሜን ማለት ምን ማለት ነው?

***አባ ዐሥራተ ማርያም፡-*** ጳጕሜን ማለት ቃሉ የጽርዕ ወይም የግሪክ ሲሆን ኤፓጎሜን ይባላል፡፡ ትርጓሜውም ጭማሪ ማለት ነው፡፡ በግእዝ ተውሳክ ይባላል፡፡ በሌላ አገላለጽ ከዐውደ ወርኀ ስለተረፈና በዓመት መጨረሻ ስለተገኘ ተረፈ ዓመት ይባላል፡፡ በዓመተ ዑደተ ፀሐይ አንድ ዓመት ፫፻፷፭ ቀናት ነው፡፡ ይህን ለ፴ ስናካፍል ፲፪ ይደርስና ፭ ይቀራል፡፡ እነዚህ ፭ ቀናት ጳጕሜን ተብለው ስለሚጠሩ ጳጕሜን ማለት ጭማሪ ወይም ተረፈ ዓመት ተብሎ ይጠራል፡፡

***ሐመር፡-*** አባታችን ከዚህ ጋር ተያይዞ ጳጕሜን ሦስቱን ዓመታት አምስት አምስት ቀናት ሆነው ሲውሉ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ደግሞ ስድስት ቀን ይሆናል፡፡ ምክንያቱን ቢያብራሩልን?

***አባ ዐሥራተ ማርያም፡-*** ይህ የሚሆንበት ምክንያት ከእያንዳንዱ ዓመት ተጨማሪ ስድስት ስድስት ሰዓት ትርፍ አለ፡፡ ይህ ስድስት ሰዓት በዐራተኛው ዓመት ፳፬ ሰዓት (አንድ ቀን) ይሆናል፡፡ በዘመነ ሉቃስ ጳጕሜን ስድስት የሚሆነው በየዓመቱ የተረፉት ስድስት ስድስት ሰዓታት ተደምረው አንድ ቀን ሲለሚሞሉ ነው፡፡

***ሐመር፡-*** በጳጕሜን ወር ሰዎች ይጠመቃሉና ምክንያቱ ምንድነው?

***አባ ዐሥራተ ማርያም፡-*** ይህን በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ከኢዮብ ጋር ተያይዞ ሲተላለፍ የመጣ ነው፡፡ ኢዮብ በደዌ ሥጋ በተመታ ጊዜ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ከደዌው ተፈወሰ፤ አዲስ ማንነትንም አገኘ፡፡ ዛሬም ሰዎች በዚያ ልማድ አምስቱንም ወይም ስድስቱንም ዕለታት በአካባቢያቸው ወደ ሚገኘው ወንዝ እየሄዱ ይጠመቃሉ፡፡ አዲሱን ዓመት በአዲስ መንፈስ ለመቀበል ሲሉ የሚያደርጉት ነው፡፡ ታሪካዊ አመጣጡ ኢዮብን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

ሁለተኛው ግን በዚህ በጳጕሜን ወር ሁለት ዐበይት ነገሮችን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ እነርሱም አንደኛው ርኅወተ ሰማይ ሲሆን፣ ሁለተኛው የሊቀ መልአኩ የቅዱስ ሩፋኤል ዓመታዊ በዓል ነው፡፡ ርኅወተ ሰማይ ሲባል በሰማይ መከፈት መዘጋት ኑሮበት አይደለም፡፡ እስጢፋኖስ የእግዚአብሔርን ክብር ባየ ጊዜ ሰማይ ተከፍቶ አየሁ በማለት እንደተናገረው ዓይነት ነው፡፡ በሐዋርያት ሥራ "በእስጢፋኖስም ላይ መንፈስ ቅዱስ መላ፤ ወደ ሰማይም ተመለከተ፤ የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየ፡፡ እነሆ ሰማይ ተከፍቶ የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ" (ሐዋ.፯፥፶፭-፶፮) ተብሎ እንደተጻፈ የማይታይና የማይገለጥ ምሥጢር ተገልጦ ሲታይ ሰማይ ተከፈተ ተባለ፡፡ እንደዚሁ ሁሉ የእግዚአብሔር ምሕረት ቸርነት ወደ ሰው፣ የሰው ጸሎት ልመና ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ የመልአኩ የቅዱስ ሩፋኤልን ዓመታዊ በዓልም የምናከብረው በዚህ ወር ውስጥ ማለትም በጳጕሜን ፫ ነው፡፡ በዚህ ዕለት የቅዱስ ሩፋኤል በዓለ ሢመት ነው፡፡ እንዲሁም በዚህ ዕለት የጸለይነውን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ያደርስልናልና እናከብረዋለን፡፡

በዚህ ዕለት ዝናም የዘነመ እንደሆን ሰዎች ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ እንፈወሳለን ብለው ስለሚያምኑ ይጠመቃሉ:: ከላይም እንደተገለጸው ርኅወተ ሰማይ ማለት የሰው ጸሎት ልመና ወደ እግዚአብሔር ሲደርስ የእግዚአብሔር ቸርነት፣ ምሕረት፣ ፈውስ ወደ ሰው ይደርሳል:: ሰው የሚጠመቀውም ለመፈወስ ነው:: ይህ ማለት የእግዚአብሔርን ምሕረት፣ ቸርነት ለማግኘት ማለት ነው:: ስለዚህ በዚህ በጳጐሜን ወር የሚደረገው ጥምቀት በቅዱስ ሩፋኤል ስም በፈለቀ ጠበል የሚደረግ ጥምቀት ማለት ነው::

***ሐመር፡-*** *ጳጕሜንን በዚህ መልኩ ከተመለከትን ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዕንቍጣጣሽም አለና እስኪ ምንነቱን ቢያስረዱን?*

***አባ ዐሥራተ ማርያም፡-*** ዕንቍጣጣሽ የተለያየ ትርጕም አለው፤ የተወሰነውን ለመጥቀስ ያህል፡- አበባ፣ ዕንቍዕ ዕፅ አወጣሽ፣ ዕንቍዕ ዕጣ ወጣሽ፣ ዕንቁ ለጣጣሽ ማለት ነው:: እያንዳንዱ ለምን እንዲህ እንደተባለ ዘርዘር አድርጎ ማየት ስለሚያስፈልግ ከላይ በተጠቀሱበት ቅደም ተከተል እንመለከት፡-

## ሀ. ዕንቍጣጣሽ

አበባ ማለት ነው:: ዕንቍጣጣሽ አበባ የሚባለው እንደሚታወቀው ይህ ወቅት አበባ የሚፈነዳበት ነው:: አበባ ለፍቅር፣ ለደስታ መግለጫ ስጦታ ሆኖ ስለሚሰጥ ለአዲስ ዓመትም ስጦታ መስጠት የተለመደ ነው:: በአዲስ ዓመት ልጃገረዶች ለታላላቅ ሰዎች የሚሰጡት ስጦታ አበባ ሲሆን ዕንቍጣጣሽ ሰጡን ይባላሉ:: ያልሰጡትንም ዕንቍጣጣሽ ሰጠሽ? እየተባባሉ ይጠያየቃሉ:: በሚሰጡበትም ጊዜ ዕንቍጣጣሽ በማለት ይሰጣሉ:: አበባ እነሆ እንደማለት ነው:: ስለዚህ ዕንቍጣጣሽ ማለት አንደኛው ትርጕም አበባ ማለት ነው::

## ለ. ዕንቍጣጣሽ

ዕንቍዕ ዕፅ አወጣሽ፡- ሁለተኛው ትርጕም ዕንቍዕ ዕፅ አወጣሽ ማለት ሲሆን ከኖኅ ዘመን ክሥተት ጋር የተያያዘ ነው:: ኖኅ የመጣውን የጥፋት ውኃ በመርከብ ሆኖ ካለፈ በኋላ እየቀነሰ ሲሄድ መርከቧም ከአራራት ተራራ ላይ አርፋ ነበርና መሥዋዕት ሠውቶ መጉደል አለመጉደሉን ለማወቅ አስቀድሞ ቁራን ላከው:: በዚያው ሳይመለስ ቀረ:: ዛሬ በሀገራችን የቁራ መልክተኛ የሚባለው ከዚያ ጋር ተያይዞ ነው:: ርግብን ሲልካት ፍሬ ያለው አበባ ቆጽለ ዕፀ ዘይት አመጣች፤ የወይራ ቅጠል ማለት ነው:: በዚህ ጊዜ ኖኅ ውኃው እንደጎደለ ስለተረዳ ከመርከብ ወጣ:: ምድር ለምልማ፣ አጊጣና አምሮባት ሲያገኛት "ዕንቍዕ ዕፅ አወጣሽ" በማለት ተናገረ:: እኛም ዛሬ ክረምቱ አልፎ ምድር ለምልማ፣ በአበባ አጊጣና አምሮባት የምትታይበት ወቅት ስለሆነ እንቁጣጣሽ እንላለን::

## ሐ. ዕንቍ ዕጣ ወጣሽ ማለት ነው፡-

ይህም ከኖኅ ልጆች ጋር የተያያዘ ታሪክ አለው:: ታሪኩም ኖኅ ከጥፋት ውኃ በኋላ በመልአኩ ዳኝነት በዕጣ ርስት ሲያከፋፍል ለካም ወደ አፍሪካ ደረሰውና የካም ልጅ ኩሽ ወደ ኢትዮጵያ መጣ:: ኢትዮጵያን ሲያገኛት እጅግ የለመለመች መልካም ሀገር ሆና አገኛት:: በዚህ ጊዜ "ዕንቍ ዕጣ ወጣሽ" በማለት ደስታውን ገለጸ::

## መ. ዕንቍዕ ለጣጣሽ ማለት ነው።

የመጨረሻው ከንግሥተ ሳባ ጋር የተያያዘ ነው:: ይህም ንግሥተ ሰባ የሰሎሞንን ዝና ሰምታ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ይዛ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደች:: እርሷ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ ንጉሥ ሰሎሞንን ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ጠይቃ የጠየቀቻቸውም ጥያቄዎች ተመልሰውላት እንደተመለሰች በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ፲፥፩-ፍጻሜ የተጻፈ ሲሆን አባቶች ከዚህ ጋር አያይዘው በታሪክ መዝገብ ተጽፎ ባይገኝም በትውፊት አባቶች የሚናገሩት ታሪክ አለ:: እርሱም ከሰሎሞን ጋር ተገናኝታ፣ ለእርሱ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን አበርክታ፣ እንቆቅልሿ ተፈቶላትና ቀዳማዊ ምኒልክን ፀንሳ ስትመለስ እርሱም በፈንታው "ዕንቁ ለጣጣሽ፣ ለቤትሽ ጣጣ ይሁንሽ" ብሎ ዕንቍዕ ሰጥቶ ሰደዳት:: ስለዚህ ዕንቍዕ ለጣጣሽ ማለት ነው ተብሎ ይተረካል::

***ሐመር፡-*** *አባታችን ዕንቍጣጣሽ አንዳንዴ የዘመን መለወጫ እየተባለም ይጠራልና ትክክለኛው ስያሜ ይህ ነው ማለት ይቻላል? ከተቻለ ቢገልጹልን::*

*አባ ዐሥራተ ማርያም፡-* በአጠቃላይ ዕንቍጣጣሽ ማለት ከላይ የዘረዘርናቸውን ትርጕሞች የሚይዝ ሲሆን በስያሜ ደረጃ አዲስ ዓመት፣ ቅዱስ ዮሐንስ፣ ርእሰ ዐውደ ዓመት ወዘተ እየተባለ ይጠራል፡፡ የስያሜው ጉዳይ ሳይሆን ለምን እንደዚህ ተብሎ ይጠራል የሚለው ነው መታየት ያለበት፡፡

ርእሰ ዓውደ ዓመት የተባለው በዘመኑ መለወጫ የሚውል የመጀመሪያው ዓመታዊ በዓል ስለሆነ ነው፡፡ ለዚህ ሊቁ ቅዱስ ያሬድም "ርእሰ ዐውደ ዓመት ዮሐንስ ወላዴ መጥቅዕ ወአበቅቴ፣ መጥቅዕንና አበቅቴን የሚወልድ የዐውደ ዓመት ሁሉ ራስ ዮሐንስ" ብሎ ነው ገለጸው፡፡ በዚህ ዕለት መገበሪያ፣ ወይን፣ ዕጣን ወዘተ ቀርቦ ጸሎተ ዕጣን ይደገማል፤ ሊቃውንቱ ባሕረ ሐሳብ ያወጣሉ፤ በባሕረ ሐሳብ የሚወጡት የዓመቱ በዓላትና አጽዋማት ተሰልተው ይታወጃሉ፡፡ ስለዚህ ርእሰ ዐውደ ዓመት ተብሎ ይጠራል፡፡ የበዓላትና የአጽዋማት ራስ መገለጫ፣ መታወቂያ ማለት ነው፡፡

ሌላኛው ስያሜ ቅዱስ ዮሐንስ ነው፡፡ ይህ ስያሜ የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ምትረተ ርእስ መስከረም ሁለት ስለሚታሰብ ከዚህ ጋር አያይዞ ለመግለጽ ነው፡፡ ምትረተ ርእሱን ለማስታወስ ቅዱስ ዮሐንስ "ዋርሳ አትውረሱ" እያለ ሲያስተምር ሄሮድስንም "የወንድምንህን የፊልጶስን ሚስት ታገባ ዘንድ አይገባህም" እያለ ስለገሠጸው አስሮት ነበርና የልደት በዓሉን በሚያከብርበት ጊዜ የሄሮድያዳ ልጅ በዘፈን አስደሰተችው፡፡ በዚህ ጊዜ ከደስታው ጽናት የተነሣ የለመንሽኝን ሁሉ አደርግልሻለሁ አላት፡፡ እናቷን ብታማክር የዮሐንስን ራስ ቆርጦ ይስጥሽ አለቻት፡፡ በዚህ ጊዜ እንቢ እንዳይላት የገባው ቃል አስጨነቀው፡፡ እሺ እንዳይላት ዮሐንስን እንደ ነቢይ ይቆጥሩት ነበርና ሕዝቡን ፈራ፡፡ ይሁን እንጂ "ሕዝቡን በጦር እታገለዋለሁ" ብሎ የዮሐንስን ራስ አስቆርጦ ሰጣት፡፡ ይህ የሆነበት መስከረም ሁለት ቀን ስለሆነ በዓሉን ከዚያ ጋር አያይዞ ለማክበር አዲሱን ዘመን ቅዱስ ዮሐንስ ብለን እንጠራዋለን፡፡

ከላይ የተገለጸው አንደኛው ምክንያት ሲሆን በዋናነት ግን ቅዱስ ዮሐንስ ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት ቅዱስ ዮሐንስ መንገድ ጠራጊ ይባላል፡፡ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት ከስድስት ወር አስቀድሞ የሰበከ፤ እኔ የጫማውን ማሰሪያ እፈታ ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በፊት የነበረው ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ነው፡፡ "እኔ ለንስሓ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን ለመሸከም የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል" (ማቴ.፫፥፲፩) እያለ ያስተማረ የሐዲስ ኪዳንን መምጣት የነገረ ነቢይ ወሐዋርያ ነው፡፡ እርሱ የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ ድልድይ ነው፡፡ ስለዚህ አበው ከአሮጌው ዘመን ወደ ሐዲሱ ዘመን የምንሸጋገርበትን ዘመን በቅዱስ ዮሐንስ ሰይመውታል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ከብሉይ ኪዳን ወደ ሐዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ እንደሆነ ሁሉ በቅዱስ ዮሐንስ የተሰየመው የእኛም አዲስ ዓመት ከክረምት ወደ መፀው የምንሸጋገርበት ነው፡፡ ስለዚህ የሐዲሱ ዓመትና የአሮጌው ዓመት መሸጋገሪያ ቅዱስ ዮሐንስ ይባላል፡፡

**ቅዱስ ዮሐንስ ከብሉይ ኪዳን ወደ ሐዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ እንደሆነ ሁሉ በቅዱስ ዮሐንስ የተሰየመው የእኛም አዲስ ዓመት ከክረምት ወደ መፀው የምንሸጋገርበት ነው። ስለዚህ የሐዲሱ ዓመትና የአሮጌው ዓመት መሸጋገሪያ ቅዱስ ዮሐንስ ይባላል።**

***ሐመር፡-*** አባታችን ይህ ስያሜ ከአራቱ ወንጌላውያን አንዱ በሆነው ዮሐንስ የተሰየመ ነው ብለው የሚያስቡ ሊኖሩ ይችላሉ ደግሞም አሉና ይህን ቢያብራሩልን?

***አባ ዐሥራተ ማርያም፡-*** አራቱ ወንጌላውያን ዘመኑን ለአራት ተከፋፍለው እየተፈራረቁ ምግብናቸውን ያከናውናሉ፡፡ በየራሳቸው ዘመን ዘመነ ማቴዎስ፣ ዘመነ ማርቆስ፣ ዘመነ ሉቃስና ዘመነ ዮሐንስ እየተባሉ ይጠራል፡፡ ከስያሜያቸውም በወንጌልም አጉልተው ከጻፉት አንጻር የየራሳቸው ምሳሌ አላቸው፡፡ ማቴዎስ በገጸ ሰብእ፣ ማርቆስ በገጸ አንበሳ፣ ሉቃስ በገጸ ላህም፣ ዮሐንስ በገጸ ንስር ይመሰላሉ፡፡ የአዲስ ዓመት ስያሜ ቅዱስ ዮሐንስ ተብሎ የሚጠራው በመጥምቁ ዮሐንስ እንጂ በወንጌላው ዮሐንስ አይደለም፡፡ ይህ ከላይም እንደተገለጸው መጥምቁ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን እና የሐዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ ድልድይ ነውና የዘመኑም ስያሜ ክረምት አልፎ በጋው የሚተካበት ስለሆነ አሮጌው ዘመን አልፎ ሐዲሱን ዘመን የምንቀበልበት ዓመታዊ በዓል በመጥምቁ ዮሐንስ ተሰይሟል፡፡

***ሐመር፡-*** አባታችን የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ ለምን በመስከረም ሆነ? ለምን እንደሌሎች በታኅሣሥ ወይም በሌላ ወር አልሆነም?

እንግዲህ በመጽሐፍ እንደሚታወቀው እስራኤላውያን ከግብፅ ከ፬፻፴ የመከራ ዘመናት በኋላ ወጥተው፣ በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት፣ በሙሴ መሪነት ባሕር ተከፍሎላቸው፣ ጠላት ተገድሎላቸው ሲወጡ ይህን ነፃ የወጡበትን ዕለት የአዲስ ዓመት መለወጫ አድርገውታል፡፡ ይህ ወር ሚያዝያ ነው፡፡ ከመከራ የወጣንበት ነው፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን የተሸጋገርንበት ነው ለማለት ነው፡፡

እንደዚህ ሁሉ የእኛም አዲስ ዓመት በረከታቸው ይድረሰንና የቀደሙ አባቶቻችን እንዳስተማሩን የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ በመስከረም የሆነበትን ምክንያት፤ ክረምት የመከራ፣ የጨለማና የሥቃይ ምሳሌ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ መከራ የምንሸጋገርበትን፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን የምንወጣበትን ወቅት አዲስ ዓመት ብለን እናከብራለን በማለት ያስረዳሉ፡፡ ደግሞም ከላይም እንደተገለጸው መስከረም ማለት ምስየተ ክረምት፣ የክረምት መካተቻ፣ ማለት ነውና ክረምቱ አልፎ ምድር በአበባ የምታሸበርቅበት ወቅት ሲመጣ አዲስ ዓመት እናከብራለን፡፡ ቅዱስ ያሬድም "ኃለፈ ክረምት ቆመ በረከት ተሠርገወት ምድር በሥነ ጽጌያት፣ ክረምት አለፈ፤ በረከት ተተካ፤ ምድርም በአበቦች አጌጠች" ብሎ እንደገለጸው ምድር የምትፈካበት፣ በአበቦች የምታጌጥበት፣ እውነትም አዲስ ዘመን የምናይበት ነውና በዚህ ወቅት ተደርጓል፡፡

አዲስ ዓመት ማለት አዲስ ነገር ስናይ ነውና በውኃ ተሸፍና የነበረችው ምድር ውኃዋ ጎድሎላት፣ ዕፀዋቱ ለምልመው አብበው፣ አሸብርቀው ለምድር ጌጥ ሆነው፣ ሙላቱ፣ ጨለማው፣ ጭቃው፣ መከራው አልፎ በአበባ ያሸበረቀች ምድር፣ በዕፅዋት ልምላሜ የፈካች ምድር የምናይበት ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ኖኅ በውኃ ተሸፍና የነበረችው ምድር ውኃው ጎድሎላት በልምላሜ አጊጣ፣ አብባ ሲመለከታት ዕንቍ ዕፅ አወጣሽ እንዳላት እኛም በውኃ ሙላት ስትናጥ የነበረችው ምድር በልምላሜ፣ በአበባ ወዘተ አጊጣ ስንመለከት እነዚህን አበቦች እያየን የምንደሰትበት ወቅት ነውና በዚህ ወቅት አዲስ ዓመት ብለን እናከብራለን፡፡

***ሐመር፡-*** አባታችን ጊዜዎን ሰጥተው ላቀረብንልዎ ጥያቄ ተገቢ የሆነውን መልስ ስለሰጡን እግዚአብሐሔር ያክብርልን፤ የአገልግሎት ዘመንዎን ይባርክልን፤ ቃለ ሕይወት ያሰማልን፡፡

***አባ ዐሥራት፡-*** አሜን እናንተንም እግዚአብሔር ይባርክልን፣ ማኅበሩን ይጠብቅልን፡፡

# “ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁላቸው”

(፩ቆሮ.፱፥፳፪)



በመ/ር ተስፋ ማርያም ቢሰጥ

በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ አንዳችን ለአንዳችን እንዴት መኖር እንዳለብን የቅዱስ ጳውሎስንና የሌሎችን ቅዱሳን ሕይወት መሠረት በማድረግ ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ የቀደመ ማንነቱን በመተው ምርጥ ዕቃ ከተባለ በኋላ ወንጌል በማስተማር የተበተኑትን በመሰብሰብ የደካሞችን ድካም ተሸክሟል፡፡ ክርስቶስ የእኛን ድካም ተሸክሞ በዚህ ዓለም ሲኖር በኋላም በመስቀል ሲገልጸው አንድም ቀን ራሱን ደስ እንዳላሰኘ ይህም ሐዋርያ በተመሳሳይ የክርስቶስን ፈለግ በመከተል እንዲህ አለ፡፡ “የሚገባስ እኛ ብርቱዎች ደካሞችን በድካማቸው እንድንረዳቸው ነው፤ ለራሳችንም አናድላ፡፡ ሁላችንም በእውነትና በመልካም ሥራ ይታነጽ ዘንድ ለባለንጀራችን እናድላ፡፡ ክርስቶስም አንተን የነቀፉበት ነቀፋ በእኔ ላይ ደረሰ ብሎ መጽሐፍ እንደተናገረ ለራሱ ያደላ አይደለም፡፡” (ሮሜ ፲፭፥፩-፪) ብሏል፡፡

የክርስትናን አኗኗር ስንኖር ራሳችንን ለመጥቀም ብቻ ሳይሆን ሌላውን ለመጥቀምና ለማስደሰት መሆን አለበት፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ ስንኳን የራሱን ጥቅም አይፈልግ” (፩ቆሮ.፲፥፳፬) በማለት እንዳስተማረን ከራሳችን ይልቅ ሌላውን ለመጥቀምና ለማስደሰት መትጋት ይኖርብናል፡፡ ገታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን በተግባር አሳይቶናል፡፡ እሱ ተሰዶ እኛን ከተሰደድንበት መለሰን፡፡ የማይራበው እሱ ተርቦ የተራብነው እኛን ሥጋውንና ደሙን በመስጠት አጠገበ፡፡ የማይጠማው ተጠምቶ የተጠማነውን እኛን ደሙን በመስጠት አረካን፤ የማይታመመው ታሞ የታመምን እኛን ከሕማመ ሥጋ በተአምራት ከሕማመ ነፍስ በትምህርት ፈወሰ፡፡

መከራ በባሕርይው የማይስማማው መከራን ተቀብሎ እኛን ከመከራ አዳነ፡፡ በፍርድ አደባባይ መቆም፣ መወቀስ፣ መከሰስ የማይገባው አምላክ በፍርድ አደባባይ በጲላጦስ ፊት ቆሞ በመወቀስ፣ በመከሰስ፣ በመገረፍ በፊቱ መቆም የማይገባን እኛን በቸርነቱ ብዛት በፊቱ እንድንቆም በማድረግ ከዘለዓለም ፍርድ በማውጣት ደስ አሰኘን ቸርነቱ ያራራዋልና ለርሱ ግን ደስታ ጎሎበት ይህን በማድረግ ደስታን አላተረፈም ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፡፡ ራሱን አሳልፎ በመስጠት የእኛን ደስታ አጸናልን፡፡ ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው “ እኔን የምትሹ ከሆነ እነዚህን ተዋቸው ይሂዱ” (ዮሐ. ፲፰፥፰) በማለት በከፈለው ዋጋ እኛን ነፃ አወጣን፡፡ እጅና እግሩን ታስሮ እኛ የታሰርንበትን የኃጢአት ሰንሰለት ቆረጠ፡፡ የእኛን ኃጢአት፤ ድካም፤. . . .በመስቀል ላይ በመሸከም ዕዳችንን፤ ሸክማችንን አቀለለ፡፡ የውርደት ሞትን በፈቃዱም ቢሆን ሞቶ እኛን ለክብር አበቃን፡፡ በአጠቃላይ ክርስቶስ ሰው በመሆኑ የፈፀማቸው ሁሉ እኛ የከበርንባቸው ናቸው፡፡

ይህም ታላቅ የወንጌል መምህር ቅዱስ ጳውሎስ “ እኔ ክርስቶስን እንደመሰልኩ እናንተም እኔን ምሰሉ” (፩ቆሮ. ፲፩፥፩) ብሎ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በመልእክቱ የጻፈው ለሌሎች እንደመኖርና የሌሎቹን ድኅነት እንደማሰብ ድካማቸውንም እንደመሸከም የሚያስደስት የለምና ነው፡፡ አንድ ሰው ብዙ ቢጾም፤ ቢጸልይ፤ ቢሰግድ፤ አርምሞ ቢይዝ የሌሎች ወገኖች ጉዳይ መራብ፣ መጠማት፣መታመምና መጎስቆል፣ በኃጢአት መውደቅ… የማያሳስበው ከሆነ ከክርስቶስ ብዙ ርቋል፡፡ ሐዋርያውም “ወንድሞቼ ሆይ የልቤ ምኞት ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበው ጸሎትም እስራኤል እንዲድኑ ነው፡፡” (ሮሜ ፲፥፩) በማለት ምኞቱና ጸሎቱ ስለሌሎች መዳን መሆኑን በአጽንኦት ይነግረናል፡፡ ሐዋርያው በልቡ እንዲህ አይነት በጎ ፈቃድ ስላለው የቆሮንቶስንም ክርስቲያኖች እንዲህ በማለት አስተማሯል “እኔ ከሁሉ ይልቅ ነጻ ስሆን ብዙዎችን ወደ ሃይማኖት እሰበስባቸው ዘንድ እንደ ባሪያ ራሴን ለሁሉ አስገዛለሁ፡፡ አይሁድን እጠቅም ዘንድ ለአይሁድ እንደ አይሁዳዊ ሆንሁላቸው፤ ከኦሪት በታች ያሉትን እጠቅም ዘንድ እኔ ራሴ ከኦሪት

በታች ሳልሆን ከኦሪት በታች ላሉት ከኦሪት በታች እንዳለ ሰው ሆንሁላቸው፤ የእግዚአብሔርን ሕግ የዘነጋሁ ሳልሆን በክርስቶስ ሕግም ሳለሁ ሕግ የሌላቸውን እጠቅማቸው ዘንድ ሕግ ለሌላቸው ሕግ እንደሌለው ሆንሁላቸው፤ ደካሞችንም እጠቅማቸው ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁላቸው፤ በሁሉ መንገድ አንዳንዶቹን አድን ዘንድ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደነርሱ ሆንሁ። በወንጌልም ትምህርት አንድነት ይኖረኝ ዘንድ ስለወንጌል ትምህርት ሁሉን አደርጋለሁ። (፩ቆሮ. ፱፥፲፱-፳፫)

ይህ ታላቅ ሐዋርያ ሰዎችን ይረዳ ይጠቅም ድካማቸውንም ይሸከም ዘንድ፤ ለአይሁዳዊውም ሕግ ለሌለውም ከሕግ በታች ላሉትም ለደካሞችም የሚያድንበትን መንገድ ለማስፋት የቻለውን አድርጓል። "እኔ ክርስቶስን እንደምመስለው እኔን ምሰሉ" (፩ቆሮ. ፲፩፥፩)ያለበት ዋነኛው ምክንያትም ይህ ነው። ክርስቶስ እኛን ከወደቅንበት ለማንሣት እያሳደድነው፣ እየደበደብነው፣ እየገፋነው እርሱ ግን እስከ ሞት ድረስ ወደደን። በመንጸፈ ደይን መውደቃችንን በእግረ አጋንንት መጠቅጠቃችንን አይቶ ልዑል ባሕርይውን ዝቅ በማድረግ እኛን ከወደቅንበት ለማንሣት ወደኛ መጥቷል። እርሱ በባሕርዩ የማይስማማውን መራብን፣ መጠማትን፣ መሰደብን፣ መገረፍን መሞትን ለኛ ሲል እንደተቀበለ እኛም ለሌሎች መዳን የቻልነውን ማደረግ ይጠበቅብናል። ቅዱስ ጳውሎስ ሌሎችን ለመጥቀም ሲል ለኅሊና የማይመቹ ብዙ ነገሮችን አድርጓል።

## ሀ. ራስን መላጨት ፡-

ቆሮንቶስ የአካይያ ዋና መዲና ስትሆን ጋልዮስ በአካይያ አገረ ገዥ በነበረበት ጊዜ አይሁድ በአንድ ልብ ሆነው በጳውሎስ ላይ ተነሡ . . ..ጋልዮስም "በዚህ ነገር ፈራጅ እሆን ዘንድ አልፈቅድም በማለት ከፍርድ ወንበር አስወጥቷቸዋል . . . . ከዚህም በኋላ ጳውሎስ እጅግ ቀን ተቀምጦ ወንድሞቹንም ተሰናብቶ በመርከብ ወደ ሶርያ ሄደ ስለትም ነበረበትና ራሱን በክርንክራኦስ ተላጨ ድርስቅላና አቂላም ከእነርሱ ጋር ነበሩ። (ሐዋ.፲፰፥፲፪-፲፰) ብፅዐት ያለበት ሰው ስድስት ቀን ከሰው ተለይቶ በሰባተኛው ቀን ጠጉሩን ተላጭቶ ገላውን ታጥቦ ልብሱን አንፅቶ መሥዋዕት አሠውቶ ማየ ምንዛህ (ውኃ) ተረጭቶ ከሰው ይገናኝ ነበር። (ዘኍ.፲፱፥፱) ቅዱስ ጳውሎስ ራሱን መላጨቱ ለእሱ ምንም ጥቅም ሳይኖረው ሌሎችን ለመሳብ አድርጓል ይህ ሐዋርያ እየተራበም እየተጠማም፤ እየተገፋም ሌሎችን ለመሳብ የሚያደርገው ጥረት እጅግ የሚደንቅ ነው።

## ለ. ግዝረት ፡-

ቅዱስ ጳውሎስ ስለግዝረት ምንነት በሰወፊው አስተምሯል "ኦሪትንም ብትፈጽም ግዝረት ትጠቅምሃለች ኦሪትን ባትፈጽም ግን ግዝረትህ አለመገረዝ ትሆንብሃለች። አንተ ሳትገዘር ብትኖር ኦሪትንም ብትጠብቅ አለመገዘርህ መገዘር ትሆንልሃለች። ተገዝረህ ኦሪትን ከምታፈርስ በተፈጥሮ ያገኘሃት አለመገዘርህ አብራህ ብትኖር ይሻልሃል፤ ኦሪት ከምታፈርስ ካንተ ከተገዘርኸው ያ ያልተገዘረው ኦሪትን የሚፈጽመው ይሻላል።... " (ሮሜ ፪፥፳፭-፳፱) በማለት በሐዲስ ኪዳን ግዝረት ማለት በመንፈስ ቅዱስ ምላጭነት በልብ ያለውን የኃጢአት ሰንኮፍ ቆርጦ በመጣልና ሕገ እግዚአብሔርን መፈፀም እንደሆነ በግልፅ አስረዳ።

በመሆኑም መገረዝም አለመገረዝም ምንም ዓይነት ጥቅም ባይኖረውም ሌሎቹን ለመጥቀምና ድካማቸውን ለመሸከም ክርስቶስም ተገርዟል። ክርስቶስ የግዝረትን ሥርዓት የፈጸመው በግብረ መንፈስ ቅዱስ ነው። ሥርዓቱን ግን የፈጸመው የአባቶቻችን ሥርዓት አይፈጽምም ብለው በእርሱ እንዳይሰናከሉ ሠራዔ ሕግ ሲሆን ፈጻሜ ሕግም ሆኖ ተገኝቷል። ቅዱስ ጳውሎስም ደርቤንና ልሳጥልን በሚባል ቦታ በግሪክ አገር ከሲላስ ጋር በደረሰ ጊዜ ወደፊት ታማኝና ተወዳጅ ልጅ የሚሆነውን ጢሞቴዎስን አገኘና ከእርሱ ጋር ይወስደው ዘንድ ወደደ ነገር ግን በዚያ ሥፍራ አይሁድ ስለነበሩ እነርሱ ደግሞ ያልተገዘረን ሰው ደቀ መዝሙር አድርጎ ሲወስድ ቢያዩ የኦሪት ግዝረት ምንም ዋጋ የሌለው መሆኑን ተምረው እስኪያውቁ ድረስ እንዳይሰናከሉና በዚህም ምክንያት ወንጌልን ከመስማትና ሰምተውም ከማመንና ከመዳን ራሳቸውን እንዳያርቁ ለእነርሱ ሲል ገዘረው። "በዚያም ስለነበሩ አይሁድ ጢሞቴዎስን ይዞ ገዘረው" (ሐዋ.፲፮፥፩-፫)

ቅዱሳን ሐዋርያት በኢየሩሳሌም ጉባዔ አድርገው በወሰኑት ውሳኔ “ሥርዓት እንዳናከብድ ሌላም ሸክም እንዳንጨምር መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር ነውና ነገር ግን ይህን በግድ ትተው ዘንድ እናዝዛችኋለን።ለአማልክት የተሠዋውን፣ ሞቶ የተገኘውን፣ ደምንም አትብሉ፤ ከዝሙትም ራቁ፤ በራሳችሁ የምትጠሉትንም በወንድሞቻችሁ ላይ አታድርጉ ከእነዚህ ሥራዎችም ሰውነታችሁን ብትጠብቁ በሰላም ትኖራላችሁ ደኅና ሁኑ” (ሐዋ. ፲፭፥፳፰-፳፱) ብለው ወስነዋል። በዚህም ውሳኔያቸው ከአሕዛብና ከአይሁድ ወደ ክርስትና የሚመጡትን ወገኖች ሲያወዛግቡ የነበሩትን ግዝረትን በኦሪት የታዘዘውን ይህን ካሉ ይህን አትብሉ የሚለውን ገለጹ። ቅዱስ ጳውሎስም አላስፈላጊነቱን እርሱም ባለበት በኢየሩሳሌም ጉባዔ የተወሰነውንና ብዙ ጊዜም በመልእክታቱ ምንም ጥቅም እንደሌለው የተናገረበትን ግዝረትን ለጊዜው ከሰዎች ደካማነት የተነሣ የእነርሱን ድካም በመሸከም ይህን ፈጽሟል። ቅዱስ ጳውሎስ በክርስትና ሕይወት ውስጥ ለራሱ ሳይሆን ለሌላው በመኖር ጨውም ቅመምም በመሆኑ መራራ በነበሩ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ክርስትናውን አጣፍጦታል።

**የክርስትናን አኗኗር ስንኖር ራሳችንን ለመጥቀም ብቻ ሳይሆን ሌላውን ለመጥቀምና ለማስደሰት መሆን አለበት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ ስንኳን የራሱን ጥቅም አይፈልግ” (፩ቆሮ.፲፥፳፬) በማለት እንዳስተማረን ከራሳችን ይልቅ ሌላውን ለመጥቀምና ለማስደሰት መትጋት ይኖርብናል።**

## ሐ. ገንዘብ አለመውደድ (አለመቀበል) ፡-

አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ወደ ዓለም ሲልካቸው ምንም ነገር መያዝ እንደሌለባቸው “በመቀነታችሁ ወርቅ ወይም ብር ወይም መሐለቅ አትያዙ። ለመንገድም ስልቻ ወይም ሁለት ልብስ ወይም ጫማ ወይም በትር አትያዙ ለሠራተኛ ዋጋው ይገባዋልና ” (ማቴ.፲፥፲) በማለት በሔዱበት የዕለት ምግባቸውን እንዲያገኙ እንጂ ሌላ ነገር እንዳይዙ አዟል። ቅዱስ ጳውሎስ ግን ቃለ እግዚአብሔርን ከሚመግባቸው ምእመናን ለዕለት ኑሮው የሚያስፈልገውን ምግብ ማግኘት መብቱ ቢሆንም ከእነርሱ ምንም ገንዘብ ሳይቀበል ድንኳን እየሰፋ ይተዳደር ነበር። ምክንያቱም ሰው ገንዘብ አምጣ ሲሉት ፊቱ ይጠቁራል ውስጡም ይቀየማል። ስለዚህ ገንዘብ ወዳድ ሆኖ የነርሱን ቢቀበል የሚያስተምረውን ወንጌል በንጹሕ ልብ እንዳይቀበሉ እንቅፋት ይሆንብኛል ብሎ ወንጌልን መስበክ ወደደ።

በተለይም ለቆሮንቶስ ሰዎች “ እነሆ ወደ እናንተ ልመጣ ስዘጋጅ ይህ ሦስተኛዬ ነው፤ ነገር ግን አልተፋጠንሁም ገንዘባችሁን ያይደለ እናንተን እሻለሁና፤ ወላጆች ለልጆች እንጂ ልጆች ለወላጆች ገንዘብ ሊያከማቹ አይገባቸውምና እኔ ግን ስለነፍሳችሁ ገንዘቤን በብዙ ደስታ እከፍላለሁ።” (፪ቆሮ.፲፪፥፲፬-፲፭) በማለት እንኳንስ የእነርሱን ገንዘብ ሊቀበል ድንኳን ሰፍቶ የሚያገኘውን ገንዘቡንና ራሱንም ጭምር ለእነሱ እንደሚከፍል በግልጽ ነግሯቸዋል። ይህንም የተናገረበት ምክንያት የቆሮንቶስ ምእመናን ገንዘብን ከመውደዳቸው የተነሣ ብዙዎች ዳኞች ባለሥልጣናት ገና አረማውያን በነበሩበትና ክርስትና ገና እየተስፋፋ በነበረበት ጊዜ እነዚህ ክርስቲያኖች “ ክርስቶስ አባታችን መንግሥተ ሰማይ ርስታችን ሀገራችን በሰማይ እያሉ በዚህ ዓለም ገንዘብ እየተጨቃጨቁ ይካሰሳሉ” እያሉ ክርስትናን ያስነቀፉ ስለነበር ነው። “ይህንም የምላችሁ ስዘልፋችሁ ነው፤ እንግዲህ ከመካከላችሁ ወንድማማቾችን ከወንድሞቻቸው ጋር ማስታረቅ የሚችል ሽማግሌ የለምን? ነገር ግን ወንድም ከወንድሙ ጋር ይካሰሳል፤ ይህም በማያምኑ ፊት ይደረጋል። እንግዲህ ጸብና ክርክር ካላችሁ ከመጀመሪያው ጀምሮ ውርደት እንደሚሆንባችሁ ዕወቁ፤ እንግዲያማ እንዴት አትነጠቁም? እንዴትስ አትገፉም? አሁንም ቢሆን እናንተ ዐመፀኞችና ቀማኞች ናችሁ፤ እንደዚህም ወንድሞቻችሁን ትበድላላችሁ።” ያለበት ምክንያት ይህን ለመግለጽነው (፩ቆሮ.፮፥፯-፰)

በኃላፊ ጠፊ ገንዘብ ምክንያት ከወንድም ጋር መካሰስ ተገቢ እንዳልሆነ በግልፅ ጻፈ፡፡ የዋሁ ጳውሊም ከወንድሙ ጋር በገንዘብ ተካሶ ሲሄድ ሬሳ ለቀብር ሰዎች ተሸክመውት በማየት ለዚህ ነው ወንድሜን የምከሰው ወንድሜ ተመለስ ሁሉ ላንተ ይሁን ብሎ ይችን ዓለም በምናኔ ተሰናብቶታል፡፡ ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስም በገንዘብ ፍቅር ከሚቃጠሉና ከሚካሰሱ ሰዎች ምንም ነገር መቀበል ያልፈለገው፡፡ ይልቁንም እርሱ ወንጌልን እያስተማራቸው ልጅነት፤ ጥምቀት፤ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር እየመራቸው የድካሙን ዋጋ የዕለት ጉርሱን ቢቀበል መብቱ እንደሆነም አስረድቷቸዋል፡፡ "ልንበላና ልንጠጣ መብት የለንም? ወይስ ሥራ ለመተው መብት የሌለን እ ኔና በርናባስ ብቻ ነን? ከቶ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማነው? ወይስ ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ ማነው? ወይስ መንጋ እየጠበቀ ከመንጋው ወተት የማይጠጣ ማነው? ይህን በሰው ሥልጣን ብቻ እላለሁ ? ሕግስ ደግሞ ያን አይልምን የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር ተብሎ በሙሴ ሕግ ተጽፏል፡፡ እግዚአብሔር ስለበሬዎች ይገደዋልን ?ይህን የሚለው ስለ እኛ አይደለምን? የሚያርስ በተስፋ ሊያርስ የሚያበራይም እንዲከፍል በተስፋ ሊያበራይ ስለሚገባው በእውነት ስለኛ ተጽፏል፡፡ እኛ መንፈሳዊ ነገር የዘራንላችሁ ብንሆን የእናንተን ሥጋዊ ነገር ብናጭድ ትልቅ ነገር ነውን በመቅደስ የሚያገለግሉ ከመቅደስ የሚሆነውን ነገር እንዲመገቡ በመሠዊያውም የሚጸኑ ከመሠውያው እንዲካፈሉ አታውቁምን ?እንዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጓል፡፡ እኔ ግን በዚህ ሁሉ ምንም አልተጠቀምኩም እንዲህ እንዲሆንልኝ ይህን አልጽፍም፡፡" (፩ቆሮ.፱፥፯-፲፩፣፲፫-፲፭)

ይህን ካለ በኋላ ለምን በዚህ መብት እንዳልተጠቀመ ሲገልጽ "በእኛ ሹመት ሌላ የሚቀድመን ከሆነ የሚሻላችሁን እናንተ ታውቃላችሁ እኔ ይህን አልፈለግሁትም፡፡ ነገር ግን የክርስቶስን ትምህርት እንዳላሰናክል በሁሉ እታገሣለሁ" አለ፡፡ (፩ቆሮ.፱፥፲፪) ይህ ታላቅ ሐዋርያ ለእርሱ የተፈቀደውን እንኳ ሳይጠቀም አሁን እኛ ባለንበት ዘመን ጓደኛ ጓደኛውን አላምን ብሎ በሩን ዘግቶ ለራሱ ብቻ ከመኖር ይልቅ በዚህ በክፉ ወቅት አንዱ የአንዱን ድካም ቢሸከም እጅግ መልካም ነበር፡፡ ምክንያቱም የአንዱ መኖር ለሌላው እጅግ ወሳኝ ነውና፡፡ መቼም ሕዝብ ሳይኖር ወታደር፤ ወታደር ሳይኖር መንግሥት ለማን ይነግሣል፡፡ ሕዝብ ሳይኖር ሀገር፤ ሀገር ሳይኖር ሕዝብ ምን ይሆናል? ገበሬ ሳይኖር በሬ ማርባት ለእርድ ብቻ ነው የሚሆነው ስለዚህ ምርት የለም ማለት ነው፡፡ ምርት ሳይኖር ገበሬው ኑሮ፤ ገበሬ ሳይኖር የከተማ ኑሮ የእምቧይ ካብ ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህ የአንዱ መኖር ለሌላው መኖር መሠረት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡-

የትንሹ ዓሣ በትልቁ ዓሣ ነባሪ በሻርኩ ላይ መኖር፡- ዓሣ ነባሪው ሲመገብ የሚተርፈውን እርሱ ይመገባል፤ ለዓሣ ነባሪው የፅዳት ሥራ ይሠራል፤ ለራሱ ደግሞ የዕለት ምግቡን ከማግኘት በዘለለ በሌሎቹ ምግብ ፈላጊዎች እንዳይዋጥ ጉዳት እንዳይደርስበት ይረዳዋል፡፡ ይህም ሂደት የጋራ ጥቅም ተብሏል፡፡ ይህም እርስ በርስ መጠቃቀም ማለት ሲሆን የትንሹን ዓሣ ድካም ዓሣ ነባሪው ተሸክሞ ሲኖር ድካም ተሰምቶት አያውቅም፡፡ ምክንያቱም ስንት ኪሎ ግራም የሚመዝን የራሱን ክብደት ተሸክሞ ይኖራል፡፡ ስለዚህ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ የደካሞችን ድካም ተሸክሞ ማለፍ በዓላማው ዝለት ልዩ ልዩ የዓለማችን ድክመት ያፈራረሰውን የሰው ልጅ ልቦና ማነጽ ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ የክርስትና ሕይወት ለራስ ብቻ ሳይሆን በራስ መኖር ውስጥ ስለሌላውም ጭምር የሚኖርበት ሕይወት ነው፡፡ ክርስቶስ እከብር አይል ክቡር፣ እነግሥ አይል ንጉሥ፣ እጸድቅ አይል ጻድቅ ሲሆን ክብር ያጣውን ሊያከብር፣ በጠላት እግር ሥር የወደቀውን ከጠላት አገዛዝ ነጻ ሊያወጣ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ይህን ዓለም እንዳዳነ ሁሉ እርሱን አብነት አድርገው የኖሩት ሐዋርያት፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት ሁሉ ለሰው ሲሉ ሥጋዊ ፍላጎታቸውን ትተው ሰዎች ድኅነተ ሥጋ ድኅነተ ነፍስን የሚያገኙበትን ተግባር አከናውነዋል፡፡ እነርሱ እየተራቡ ለሌላው ሲያበሉ፣ እነርሱ እየተጠሙ ለሌላውን ሲያጠጡ ኑረዋል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁላቸው" (፩ቆሮ.፱፥፳፪) በማለት የገለጸው እንዲህ ያለውን ተግባር እንድንረዳ ነው፡፡ እኛም በእንደዚህ ያለው መልካም ተግባር እንድንኖር እግዚአብሔር ይፍቀድልን፡፡

*ወስበሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር አሜን !*

# ነፍሴን የት ልውሰዳት?

## ኪነ ጥበብ

*በዲ/ን አሸናፊ ደሳለኝ*

“አጥብቄ ፈለግሁ . . . ደከምሁ፤ እጅግም ባዘንሁ፤ ዙሪያ ገባውን ሁሉ እየቃኘሁ የዓለምን ዳርቻዎች ሁሉ አማተርሁ፤ . . . ነገር ግን ነፍሴን እፎይ ብየ አሳርፋት ዘንድ እሸሽግበት ጥግ አጣሁ የደከመ መንፈሴን ሰላም አሰፍንበት ዘንድ ማረፊያ ወደብ አጣሁ . . አዎ እጅግ ባተትሁ ነፍሴን ከደካማው ሥጋየ እሥር አላቅቄ ነጻነትን አጎናጽፋት ዘንድ ማረፊያው የሥጋ ሸክም ማራገፊያው ከቶ ወዴት ነው? “ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል” (ማር. ፰፥፴፮) እንዲል ቅዱስ መጽሐፍ በዚህ ምድራዊ ዓለም የሚዳሰስ፣ የሚላስ፣ የሚቀመስ ይጣፍጥ ዘንድ ግን ከቶ በማይቻለው የዓለም ግሳንግስ የተወረረችና ዝላ የደከመች ነፍሴን ምኞት፣ ዝሙትና ፍቅረ ንዋይ የተሰኙ ወንበዴዎች ደብድበው ያቆሰሏትን ድኩም ነፍሴን ዘይቱን አፍስሶ ቁስሌን ወደሚያክምልኝ ያ ደግና ርኅሩኅ ሳምራዊ አደርሳት ዘንድ ከቶ የት ልሂድ::” (ሉቃ. ፲፥፴፫) እያሉ አባ ሞገሴ ረዘም ባለ ንግግራቸው ድምፃቸውን ጎላ አድርገው ያወራሉ::

አባ ሞገሴ ከሰው ጋር ያሉ መስሎኝ ትቻቸው ልሄድ ስል ብቻቸውን ናቸው:: አመማቸው እንዴ ብየ ልጠይቃቸው ስል ዐይናቸውን ወደሰማይ ቀና አድርገው ከነበሩበት ስሜት ማንም የሚያናውጻቸው ያለ አይመስልም:: አባ ሞገሴ በአንድ ታዋቂና ታላቅ ደብር ጸሎት አሳራጊ አባት ናቸው:: በዚህ ታላቅ ደብር ቄሰ ገበዝ ሆነው ለረጅም ጊዜ ካገለገሉ በኋላ የጸሎት አሳራጊ አባት እንዲሆኑ በካህናቱ ፈቃድ ከሰሞነኛነት ተለይተው የሚኖሩ አባት ናቸው:: ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ቅዱስ አባት ለአርባ ዓመት ቆመው የጸለዩበት ቦታ ነው ከሚባል ጫካ ቆመው እየጸለዩ ነው:: እኔም ስሜታቸውን ከምረብሽ በጽሞና ማዳመጡና ከጸሎታቸው በረከት መቀበሉ የተሻለ ነው ብየ ማዳመጥ ጀመርሁ:: አባ ከብሉያት ከሐዲሳት እየጠቃቀሱ ልመናቸውን ቀጠሉ::

ሰው መሆንን እና የሰውነትን ልክ በሚበላና በሚጠጣ በሚግብሰበስ ከንቱና ሕይወት የለሽ በድን በሆነ መስፈሪያ የሚመዝን ዓለም የታከተች ብኩን ነፍሴን አሳርፋት፤ ሰላም እሰጣት ዘንድ የት ልሂድ የት ልድረስ:: ታላቁን ቅዱስ መጽሐፍ ባገላበጥሁ ጊዜ እናንተ “ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ . . . . ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ” (ማቴ፲፩፥፳፰-፳፱) ያለውን መንፈስን የሚያድስ ልብን የሚያበረታ ቅዱስ ቃል ዓይኖቼ ተመለከቱ ትንሽ አለፍ ብየ ቅዱሱን መጽሐፍ በትኩረት ሳገላብጥ ሌላ ለጥያቄየ ምላሽ ፍንጭ የሚሆነኝን አጽናኝ ቅዱስ ቃል አስተዋልኩ “ሰላምን እተዉላችኋለሁ፡ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ:: እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም” (ዮሐ.፲፬፥፳፯):: እያሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የቅርብ ግንኙነት ስሰማ እኔም ወደ ኋሊናየ ተመለስሁ::

በዚህ ጊዜ ልቤ ሐሤት አደረገች መንፈሴም ደስታን ተመላ . . . ያች ከዐሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም ይፈሳት የነበረች ሴት (ማቴ.፺፥፲፪) የጌታችንን የልብሱን ዘርፍ ስትዳስስ የተሰማት ዓይነት የፈወስ ተስፋ በውስጤ ለመለመ ደግሞም እንደ ሳምራዊቷ ሴት (የሐ. ፬፥፱) የማውቀውን ታሪኬን ነግሮኝ ለዘለዓለም እንዳልጠማ የሚያደርገኝን የነፍሴን እረፍት እንዳገኘሁት ተሰማኝ እናማ የእርሱን የአምላኬን የጌታየንና መድኃኒቴን ጥሪ ተቀብየ የከበደ ሸክሜን አራግፌ ዓለም እንደሚሰጠኝ ያልሆነውን የዘለዓለም ጥማቴን የሚያስወግድልኝን እረፍት አገኝ ዘንድ “ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ” (መዝ. ፻፳፩፥፩) እንዲል መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት ማለዳ በትጋት ተነሥቼ የክርስቶስ ሙሽራ፤ የክርስቶስ አካል (ፊል. ፬፥፲፰) ክርስቶስ በገዛ ደሙ የዋጃት (ሐዋ. ፳፥፳፰) የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የድሆች መጠጊያ ወደ ሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በፍቅር ገሰገስሁ::

እናም በዚህ ልዩ ቀን እግሮቸ በተስፋ ከቤቴ ደጅ ተነሥተው

የማለዳውን ፀጥታና ሰላም እያጣጣሙ "ቅረቡ ኀቤሁ ወያበርህ ለክሙ ወኢይትኃፈር ገጽክሙ ወደ እርሱ ቅረቡ ያበራላችሁማል ፊታችሁም አያፍርም ይህ ችግረኛ ጮኸ እግዚአብሔርም ሰማው፤ ከመከራውም ሁሉ አዳነው" (መዝ. ፴፫፥ ፮) የሚለውን የቅዱስ ዳዊት ድንቅ መዝሙር በውስጤ እያዜምኩ ነፍሴን አሳርፋት ዘንድ በፍቅር እየተራመድኩ ወደ ቅዱስ ደጁ አመራሁ። እውነት እላችኋለሁ በማለዳ ከእንቅልፍ ድካም ተገላግለው በፀጥታው ጎዳና ወደ ደጀ ሰላሙ ሲያመሩ ያለው ጣዕም ያለው መንፈሳዊ እርካታ ከጎሊና በላይ ነው።

ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር አቅራቢያ በደረስኩ ጊዜ ኃጢአቴን እያሰብኩ ለመጸጸት . . . ልቤን አሰናዳሁ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልዩ ሰማያዊ መዓዛ ለመመሰጥ ደካማ ሥጋየን ጎስሜ እንግዲህ እግዚአብሔርን እሽ በሉት፤ ሰይጣንን ግን እንቢ በሉት፤ ከእናንተም ይሸሻል እግዚአብሔርን ቅረቡት ይቀርባችሁማል ተብሎ እንደተጻፈ ጥንተ ጠላቴን እንቢ ብየ በተመስጦ ገሰገስኩ . . . ያን ዕለት ደስታ ውስጤን እያረሰረሰኝ ነበር . . . ሄደኩ ተራመድኩ።

ነገር ግን ምን ዋጋ አለው የካራን ኑሮየን ትቼ የሲናን በርሃ አቋርጬ ጉዞየን ፈጽሜ የተስፋይቱን ምድረ ከነዓንን ሳልረግጥ . . . አንድ አስደንጋጭ ጆሮን በመውጋት የሚያሳቅቅና ልብን የሚያስበረግግ ድምፅ ወደ ጆሮየ ገባ "ጧፍ ጧፍ . . . ሻማ፣ ነጠላ፣ ድስት፣ ብረት ድስት በርካሽ ዋጋ ይዉሰዱ … ቁጤማ ቁጤማ፣ ከኢየሩሳሌም የመጣች ልዩ መስቀል በአባቶች የተባረከ. . . ወ ዘ ተ።"

በዚችው ቅጽበት ከነፍሴ ተፋትቼ ከከንቱ ሥጋዬ ጋር በድጋሜ ጋብቻ ፈጸምኩ፤ እናማ በልቡናዬ ሐሳብ ማውጠንጠን ጀመርሁ "አወ ስመለስ ቁጤማ እገዛና በጠዋት ቤቴን አጫጭሸ ሞቅ ሞቅ አድርጌ ቡናየን አፍልቼ ከጎረቤቶቼ ጋር ፈታ እላለሁ . . ." ብቻ ምን አለፋቹህ በዚያች ቅጽበት ከሰማያዊው ከፍታ ማማ እራሴን አውርጄ ስለ ማኀበራዊና ሥጋዊ ሕይወቴ ማሰላሰል እየጀመርሁ ዐውድ እየቀያየርሁ ከነፍሴ ተፋታሁ ዴማስን ሆነኩና የተሰሎንቄ ውበት ሳበኝ። ወደ ኋላ ዞሬ መንፈሳዊ የሕይወት ጉዞየ ተሰናክሎ የጨዉ ሐውልት ሆኘ ቀረሁ።

ትንሽ ከደካማው የሐሳብ ጉዞየ መለስ ስል ለካንስ ምእመናን "ለእግዚአብሔር በፍርሃት ስገዱ" ያለውን የሠራዒ ዲያቆኑን አዋጅ ሰምተው በፍርሃት ሰግደዋል . . . እግሮቼም እኔ ልብ ሳልላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ዘልቀው ገብተዋል . . . በድርጊቴ በጣም ተሳቀቅኩ አፈርኩ ተሸማቀቅሁ . . . እናም ከምእመናን ጋር ለመመሳሰል በአምልኮ እሰግድ ዘንድ ጉልበቴን ሸብረክ ሳደርግ ምእመናን ሁሉ ከሰገዱበት "ተንሥኡ" ተብለው እየተነሡ ነበር። ከትንሽ የአስተውሎትና የተመስጦ ጊዜ በኋላ ይህ ከንቱ መርጦ አድማጭ ጆሮየ ተምዘግዝጎ ከደጀ ሰላሙ ቅጽር ግቢ አፈትልኮ ወጣ . . .ሄደ.. ገሰገሰ ወደ ኋላ ነጎደ . . . ለካስ የዓለም ሁካታ ሲከንፍ ከጀርባየ ተከትሎኛል . . . አቤት . . የድምፁ መረበሽ ቀጠለ ጫጫታው "የጭንቅ ደራሿ ማሠሪያ ነው አምስት ዐሥር ያላቹህን …..የፈጥኖ ደራሹ … ጣሪያው እያፈሰሰ ነው። ዐሥር ሺህ ብር ትኬቱን ለበረከት . . ወንድማችን እገሌ …በኩላሊት በሽታ ….ወደ ውጭ ሀገር ሂዶ እንዲታከም. . . ጧፍ በአንድ ብር በአንድ ብር: ልዩ ሎተሪ በጊዮርጊስ ቀን የሚወጣ፣ ትሪ፣ ሳሃን፣ ብረት ድስትም፣ አለ ወ ዘ ተ ወ ዘ ተ" ውይ …ሲያደክም ተደበላለቀብኝ የትኛውን ትቼ የተኛውን እንደምሰማ ግራ ግብት አለኝ ነፍሴን . . . እረሳኋት. . . . ተውኳት ጭራሽ ተሰናበትኳት . . . በድንገት ስልኬን አወጣሁ፤ ሰዓቴንም በፍጥነት ተመለከትኩ፤ ሰዓቱ ሂዷል ራሴን ስለነፍሴ ሳይሆን ሰለ ሰዓቱ መሄድ ሲጨነቅ አገኘሁት … ይሄኔ ታዴያ ራሴን ታዘብኩት በመንፈስ ሳይሆን በሥጋ እንደነበርኩ ታወቀኝ።

የሥርዓተ ቅዳሴውን መጠናቀቅ ሳይሆን የሰዓቴን ጉዳይ አስቀድሜ ቅዱሱን ደጀ ሰላም በድፍረት ረጋግጬ በምእመናንና በቅዱሳን መላእክት ላይ ተረማምጄ ስከንፍና ስክለፈለፍ ወጣሁ . . . ከውስጥ ጆሮየን መስጦ ሲጠራኝ ወደ ነበረው ጎትቶ ወደ አስወጣኝ ሁካታ በፍጥነት ተቀላቀልኩ …. የሥጋ ስሜቴን በመንፈሳዊ ገበያ ሸመትኩ …. ይህ ሁሉ ሁኖ ግን ነፍሴ አላረፈችምና ሰላም አላገኘሁም . . .እንደገና ተጨነኩ እንደገና ውጥረትና መረበሽ . . . ነፍሴ ታርፍ ዘንድ እድሉን የዕለት ቀለቧን የዘመናት ምግቧን ቃለ እግዚአብሔርን ታገኝ ዘንድ አለፈቀድኩላትምና ዕረፍት አላገኘችም።

መለስ ብየ የአባ ሞገስን ተመስጦ አስተዋልኩ። ዕድሜ ልካቸውን በአገልግሎት ተጠምደው ኑረው አሁን ደግሞ የጸሎት ጊዜ ሲያገኙ ራሳቸውን እንደ ፍጹም ኃጢአተኛ ቆጥረው ማረኝ ማረኝ ይላሉ። እኔ ግን በአግባቡ ቅዳሴ ለማስቀደስ እንኳን አልበቃሁም። የአባ ሞገስን ጽናት እንደሳቸው ለመሆን ባልችልም ወደ እርሳቸው ሕይወት የሚወስደኝን መንገድ የሚዘጉብኝን ምክንያቶች እያሰብኩ እንዲህ ማለት ጀመርሁ። ደግሜ ደጋግሜ እጠይቃለሁ ዕረፍት ታገኝ ዘንድ ነፍሴን የት ልውሰዳት ፤ የነፍሴ ማረፊያ የልቤን ሰላም ሳዝን መጽናኛየን "ኢትግበሩ ቤተ አቡየ ቤተ ምስያጥ" (ማቴ. ፳፩፥፲፫) የተባለላትን እናቴን ቅድስት ቤተ ክርስትያንን የመሸጫ የመለወጫ የሌባና የቀማኛ ዋሻ ልታደርጉ በዙሪያዋ የከበባችሁ መንፈስ አልባ ሥጋ ለባሶች ከሰማያዊነቴ አርማና ምስክር ከቅድስት ቤተ ክርስትያን ትርቁ ዘንድ እለምናችኋለሁ።

አጥንትን የሚያለመልመውን ልቡናን የሚመስጠውን ሰማያዊውን የቅዱስ ያሬድን ጥዑም ዜማ አፍናችሁ የምሕረቱን ዐውድ በገንዘብ ጉዳይና ጨረታ የከፈታችሁ የሥጋ ጠበቆች ከነፍሴ መሸሸጊያ ከማረፊያ ወደቤ ወግዱልኝ። "እስመ ቅንዓተ ቤትከ በልዓኒ ትዕይርቶሙ ለእለ ይትኤየሩከ ወድቀ ላዕሌየ የቤትህ ቅናት በለታኛለችና የሚሰድቡህም ስድብ በላየ ወድቋል" (መዝ. ፷፰፥፱) እንዲል መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት አቤቱ የቤትህ ቅናት አቃጥሎኛል ነፍሴን ታሳርፋት ዘንድ ጅራፍ አንስተህ ሻጭና ለዋጮችን ከቤተ ክርስቲያን፣ ማደሪያህ ከሆነው ቤተ መቅደስ ከተባለው እኔነቴ ደግሞ ከንቱ ዓለማዊ ሐሳብን አርቀህልኝ ትንሣኤ ልቡናን አድለህኝ ምክንያተኝነቴንና ሰበበኝነቴን አሽቀንጥሬ ጥየ የነፍሴን ዕረፍት አፋጥን ዘንድ ጣቶችን ወደ ሌሎች መቀሰር ብቻ ሳይሆን ወደ ራሴም ተመልክቼ በመንፈስ እበረታ ዘንድ እርዳኝ። የነፍስ ዕረፍት ከልቡና ከሐሳብ ይጀምራልና ልቡናየን በምሕረት ከወደቀበት ታነሣልኝ ዘንድ እለምንሃለሁ አዎ ያኔ ነፍሴ ማረፊዋን ታገኛለች።

# መጻጉዕ ሕይወቴ

እምነተ ጎደሎው ሰንከልካላው ልቤ፤
የኀጢአት አውድማ ደካማው ሐሳቤ።

ለሠላሳ ዘመን ደግሞም ከዛ በላይ ፤
በደዌ ተይዞ ተኝቷል አልጋ ላይ።

ውኃውን ሲያናውጥ ቃልህ ቀስቃሽ ሆኖ ሕይወትን ሊያለብሰኝ፤
ወደ ፈዋሹ ምንጭ የሕይወት እንጀራ በፍቅር ሲጠራኝ፤
እሽ ብየ ለመሄድ መንፈሳዊ ወኔ አቅም ስላጠረኝ።

አልጋህን ተሸከም በንስሓ ታጠብ፤
ከእንግዲህ በኋላ በደልን አታስብ፤

ብለህ አበረትተህ ልዳን ፍቀድልኝ፤
አልጋህን ተሸከም ተመላለስ በለኝ።

# የቱርክ መንግሥት የሀግያ ሶፊያን ቤተ መቅደስ ወደ መስጅድነት መቀየሩን ተከትሎ ዐሥራ አራት የአውሮፓ ሀገራት ድርጊቱን እንዲያወግዙ ጥሪ ቀረበላቸው

*በካሳሁን ለምለሙ*

የቱርክ መንግሥት ታላቁንና ጥንታዊውን የሀግያ ሶፊያ ቤተ መቅደስ ወደ መስጅድነት መቀየሩን ተከትሎ ዐሥራ አራቱ የአውሮፓ ሀገራት መንግሥታት ድርጊተን እንዲያወግዙ የግሪኳ ፕሬዘዳንት ካተሪና ሳከላሮፖውሎው (Katerina Sakellarouplou) ጥሪ እንዳቀረቡላቸው ኦርቶዶክስ ታይምስ ዘግቧል። ፕሬዘዳንቷ ለዐሥራ አራት አውሮፓ ሀገራት መንግሥታት ደብዳቤ የጻፉ ሲሆን በደብዳቤያቸውም ጥንታዊውና በአውሮፓ የቀደመ ታሪክ ትልቅ ቦታ ያለውን የሀግያ ሶፊያ ቤተ መቅደስ ወደ መስጅድነት የመቀየር የቱርክ መንግሥት ውሳኔን እንዲታገሉና እንዲያወግዙት አሳስበዋል።

ታላቁ የሀግያ ሶፊያ ቤተ መቅደስ የአውሮፓውያንን የጋራ ማንነት፤ እሴትና ልዩነት ለወደፊቱ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው ያሉ ሲሆን ፕሬዘዳንቷ ቤተ መቅደሱ የአውሮፓውያን የጋራ ታሪካዊ ቅርስ፣ ልዩ ጥበብና እምነትን ያጣመረ እንደሆነም ገልጠዋል። ከዚህ ቀደም ቤተ መቅደሱ እንደ እ.ኤ.አ. ፲፱፻፹፭ ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፤ ሳይንስና ባህል ድርጅት የዓለም ቅርስ ሆኖ ተመዝግቧል። በመሆኑም የቱርክ መንግሥት ቤተ መቅደሱን የመቻቻል፣ የሰላም፣ የአብሮ መኖር፣ በባህሎችና በሃይማኖት ተቋማት መካከል የመነጋገሪያ ምልክት ሆኖ እንዲቀጥል ከማድረግ ይልቅ የግጭት፣ ያለመቻቻል፣ የመገፋፋትና የጥርጣሬ ምልክት እንዲሆን ማድረጉ እንዳስከፋቸው ፕሬዘዳንቷ ተናግረዋል።

መንግሥታቸው ድምፁን በማሰማት የቱርክን መንግሥት ድርጊት ማውገዙን እንደሚቀጥል ያስታወቁት ፕሬዘዳንቷ የቱርክ መንግሥት ጉዳዩን መልሶ እስኪያጤነውና ውሳኔውን እስኪያስተካክል ድረስ ማውገዛቸውንም እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል። ታላቁ የሀግያ ሶፊያ ቤተ መቅደስ ወደቀደመ ክብሩና ማንነቱ እስካልተመለሰ ድረስ ጥሪ የቀረበላቸው አሥራ አራቱ የአውሮፓ ሀገራት መንግሥታትም ማውገዛቸውንና ድምፃቸውን ማሰማታቸውን እንዲቀጥሉ ፕሬዝዳንቷ አሳስበዋል።

ቡልጋሪያ፣ ኦስትሪያ፣ ጀርመን፣ ኢስቶኒያ፣ አየርላንድ፣ ላቲቪያ፣ ክሮሺያ፣ ጣሊያን፤ ማልታ፣ ሀንጋሪ፣ ፓላንድ፣ ፓርቹጋል ፣ስሎቫኒያ እና ፊንላንድ ፕሬዝዳንቷ በጻፉላቸው ደብዳቤ የሀግ ሶፊያን ቤተ መቅደስ በተመለከተ የቱርክን መንግሥት እንዲያወግዙ ጥሪ የቀረበላቸው የአውሮፓ ሀገራት መንግሥታት ናቸው።

# የኢራቁ ፕሬዘዳንት ለክርስቲያኖች አስቸኳይ ጥሪ አቀረቡ

በመካከለኛው ምሥራቅ የምትገኘው የዐረቡ ዓለም ፈርጥ ኢራቅ ቀላል ለማይባሉ ዓመታት በእስላማዊው የሽብር ቡድን (አይኤስ አይኤስ) ስትታመስ መቆይቷ ይታወቃል። ሀገሪቱ እስላማዊው የሽብር ቡድን እያደረሰባት ካለው ጥቃት ለመዳን ለበርካታ ዓመታት ያለ የሌለ ኃይሏን አሟጣ ስትለፋም ኖራለች። የሽብር ቡድኑን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከግዛቶቿ ለማስወጣት ያላሰለሰ ጥረት ስታደርግ የቆየች ቢሆንም እንዳሰበችው ሳይሆን ቀርቶ ቀላል የማይባል ዋጋ አስከፍሏታል። በዚህም ምክንያት ብዙ ዜጎቿን በስደትና በሞት ተነጥቃለች። በርካታ የሀገሪቱ ግዛቶችም እንዳለሆነ ሆነው ወድመዋል። በወቅቱ ታዲያ እስላማዊው የሽብር ቡድን በሀገሪቱ የሚኖሩ ክርስቲያኖችን ዓይናችሁን ለአፈር ብሎ ያሳድዳቸውና ይገድላቸው ነበር። የማምለኪያ ሥፍራቸውንም ያወድምባቸው ነበር። ክርስቲያኖቹ

ከሕይወት መሥዋዕትነት ጀምሮ ለዘመና እስካፈሩት ሀበትና ንብረት ድረስ ለእስላማዊ የሽብር ቡድን ገብረዋል፡፡ በሕይወት የተረፉት ክርስቲያኖች ደግሞ "ከመሞት መሰንበት ይሻላል" ብለው ቀያቸውን ጥለው ተሰደዋል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ የሰላም አየር በሀገሪቱ ላይ መንፈስ ጀምሯል፡፡ ይህንን የሰላም አየር መኖሩን የረጋገጡት የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ታድያ በፀጥታ ችግር ምክንያት ሀገራቸውን ጥለው የተሰደዱትን ክርስቲያን ዜጎቻቸውን "እባካችሁን በአስቸኳይ ወደ ተውልድ ሀገራችሁ ተመለሱ" የሚል የመማጸኛ መልእክት እንዳስተላለፉ ከኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ሙስጠፋ አልካዚሚ በስደት ያሉ ክርስቲያን ዜጎቻቸውን "የሀገሪቱ ልጆች በመሆናችሁ እባካችሁ ወደ እናት ሀገራችሁ ተመለሱ" በማለት ተማጽነዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለኢራቃውያን ክርስቲያኖች አስቸኳይ የሆነውን ጥሪ ካቀረቡ በኋላ ከሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር በኢራቃውያን ክርስቲያኖች የወደፊት ዕጣ ፈንታ ዙሪያም በሰፊው መክረዋል ይላል ዘገባው፡፡

በሀገራቸው መንግሥት በኩል ጥሪ የተደረገላቸው በየዓለማቱ የሚገኙ ኢራቃውያን ክርስቲያኖች የመንግሥታቸውን ጥሪ በደስታ ተቀብለው ወደሀገራቸው ለመመለስ ፈቃደኛ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተሰበረ ልብ ውስጥ ሆነው ኢራቅ የሁሉም ሀገር እንደሆነችና በተለይም ክርስቲያኖች የሀገሪቱ ቀደምት ዜጎች እንደሆኑ ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ የበለጸገችውንና ያደገችውን የወደፊቷን ኢራቅ ለመገንባት የክርስቲያኖች ሚና በሀገራቸው ላይ የጎላ እንደሆነ ያነሡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢራቅ ያለ ክርስቲያን ልጆቿ ካሰበችው ልትደርስ እንደማትችልም አስምረው ተናግረዋል፡፡

ክርስቲያን ዜጎቻቸውን ቁርጠኛ ሆኖ ለመደገፍና ችግሮቻቸውን ለመፋታት መንግሥታቸው ዝግጁ እንደሆነ ፕሬዳንቱ ያስረዱት ሲሆን ክርስቲያኖች ወደ እናት ሀገራቸው ኢራቅ ተመልሰው መጥተው በሀገሪቱ መልሶ ግንባታ ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ጋብዘዋል፡፡ የሙስጠፋ አልከዚሚ መንግሥት ክርስቲያን ዜጎቹ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ የሚያደርገውን ውትወታ ተከትሎ የተወሰኑት ወደሀገራቸው ለመመለስ ፍላጎት ቢያሳዩም አንዳንዶች ግን እስላማዊ የሽብር ቡድን ከዚህ ቀደም ያደረሰባቸውን ሥቃይና ግድያ በማስታውስ አሁንም ደረስ የፀጥታ ችግር ይኖራል በማለት ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ፍላጎት እያሳዩ እንዳልሆነ ታውቋል፡፡

**ክርስቲያን ዜጎቻቸውን ቁርጠኛ ሆኖ ለመደገፍና ችግሮቻቸውን ለመፋታት መንግሥታቸው ዝግጁ እንደሆነ ፕሬዳንቱ ያስረዱት ሲሆን ክርስቲያኖች ወደ እናት ሀገራቸው ኢራቅ ተመልሰው መጥተው በሀገሪቱ መልሶ ግንባታ ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ጋብዘዋል፡፡**

# ቅጽል

## አቦጊዳ የግእዝ ትምህርት

በዲ/ን ዐቢይ ሙሉቀን

ቅጽል ማለት ከስም ጋር እየተጨመረ ስምን ከግብር፣ ከዓይነት፣ ከመጠን ወዘተ አንጻር የሚገልጽ ቃል እንደሆነ ባለፈው እትማችን ተመልክተናል። በዚህ ክፍል ደግሞ የቅጽል ዐይነቶችን እንመለከታለን።

### የቅጽል ዓይነቶች፡-

የቅጽል ዓይነቶች እንደየ ምሁራኑ የተለያየ አከፋፈል አላቸው። ለምሳሌ፡- አለቃ ኪዳነ ወልድ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ በተባለ መዝገበ ቃላታቸው በመጀመሪያ ዘርና ነባር ብለው በሁለት ከከፈሏቸው በኋላ በእያንዳንዳቸው ደግሞ ሌሎች ንኡሳን ክፍሎች እንዳሉ ይዘረዝራሉ። (ገጽ ፹፱-፺፩)

መምህር ኃይለ ኢየሱስ የልሳነ ግእዝ መማሪያ ብለው ባዘጋጁት መጽሐፍ ከቅርጻቸውና ከአገልግሎታቸው በመነሣት በስምንት ይከፍሏቸዋል። እነዚህን ክፍሎችም ፡- ውስጠ ዘ ቅጽላት፣ ስማዊ (ጾታዊ) ቅጽል፣ አስተአማሪ ቅጽል፣ መጠናዊ ቅጽል፣ አኃዝ ቅጽል፣ መጠይቃዊ ቅጽል፣ መተርጕም ቅጽል፣ መድበል ቅጽል ብለው ይዘረዝሯቸዋል። (ገጽ ፹፮)

መምህር አስበ ድንግል ግእዝ ልሳነ ኢትዮጵያ በተባለ መጽሐፍ "ግልጠ ዘ እና ውስጠ ዘ" በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል። መምህር አስበ ድንግል ግልጠ ዘ በሚሏቸው ውስጥ ዘን፣ እንተንና እለን ከዘረዘሩ በኋላ ሌሎችን በሙሉ በውስጠ ዘ ያካትቷቸዋል። (ገጽ ፳)

እዚህ ላይ በምሳሌነት ያቀረብናቸው ሦስቱም መምህራን ለመክፈል የተነሡበት የእይታ አንጻር (የሚከፍሉበት አንጻር) ነው እንጂ መሠረታዊ ልዩነት የሚፈጥር አይደለም። አንደኛው ከቅርጻቸው ሌላኛው ከአገልግሎታቸው ወዘተ አንጻር ስለከፈሉት ነው።

በዚህ ጽሑፍ የአለቃ ኪዳነ ወልድን አከፋፈል በመከተል ዘርና ነባር ቅጽል በሚለው መልኩ እንመለከተዋለን።

ዘር ቅጽል፡- ዘር ቅጽል ማለት መነሻ ግስ ያለው ከግስ የሚወጣ የግስ ወይም የአንቀጽ ዘር ማለት ነው። በዚህ ክፍል ማለትም ዘር ቅጽል የሚባሉት

ውስጠ ዘ፣ መስም፣ መድበል፣ አኃዝ፣ ጥሬ ዘር ይካተታሉ።

ውስጠ ዘ ፡- ይህ ማለት በውስጡ የዘን ሙያ የሚያካትት ሲሆን ግልጠ ዘዎችን ማለትም ዘን፣ እንተንና እለን ሳይፈልግ እንዲሁ የሚቀጸል ማለት ነው።

ውስጠ ዘ ደግሞ ሣልስ ውስጠ ዘ እና ሳድስ ውስጠ ዘ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ።

ውስጠ ዘ ሣልስ ውስጠ ዘ እና ሳድስ ውስጠ ዘ ተብሎ የሚከፈልበት ምክንያት የመጀመሪያው በመድረሻ ፊደላቸው ሲሆን ከትርጉም አንጻርም የተወሰነ ልዩነት አላቸው።

ለምሳሌ፡- ሣልስ ውስጠ ዘ መጨረሻው ሣልስ ፊደል የሆነ ማለት ነው። ቀዳሲ፣ ወዳሲ ፣ ጸሐፊ…

ሳድስ ውስጠ ዘ ደግሞ መድረሻው ሳድስ ፊደል የሆነ ማለት ነው። ቅዱስ፣ ውዱስ፣ ጽሑፍ…

ከትርጉም አንጻር ደግሞ ሣልስ ውስጠ ዘ በአድራጊ ማለትም ቀታሊ የሚለው የሚገድል/ የገደለ ተብሎ ሲተረጎም ሳድስ ውስጠ ዘ ግን በአምስት መንገድ ይተረጎማል። ይህ ማለት በአድራጊ፣ በተደራጊ፣ በአስደራጊ፣ በተደራራጊና በአደራራጊ ይተረጎማል። ቅቱል የሚለውን ቃል ብንወስድ የገደለ፣ የተገደለ፣ ያስገደለ፣ ያገዳደለና የተገዳደለ ተብሎ ይተረጎማል።

ሁለቱንም በዐረፍተ ነገር እንመልከት።

ሣልስ ቅጽል፡- ሐራሲ ዳዊት ይዘርዕ ዘርዐ ውስተ ገራህቱ፤ አራሹ ዳዊት ዘሩን በእርሻው ላይ ይዘራል።

ሐናጺ ቶማስ ሐነጸ ቤተ መንግሥት፤ ግንበኛ ቶማስ የመንግሥት ቤትን ገነባ።

መሓሪ እግዚአብሔር ይገብር ምሕረተ ለምእመናኒሁ፤ መሓሪው እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ምሕረትን ያደርጋል።

ሳድስ ቅጽል፡- ስቡሕ እግዚአብሔር ይሴባሕ በአፈ ኵሉ ፍጥረት፤ ምስጉን እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ አንደበት ይመሰገናል።

ቅቱል ዳዊት አስተፍሥሐሙ ለሰብአ አይሁድ፤ የገደለ ዳዊት ሰብአ አይሁድን አስደሰታቸው።

እቡይ ጎልያድ ኢክህለ ቀቲለ ዳዊትሃ፤ የሚመካ ጎልያድ ዳዊትን መግደል አልቻለም።

ውድ አንባብያን የሚቀሩትን የውስጠዘ የቅጽል ዓይነቶችን በሚቀጥለው እንመለከታለን።